# ትምህርተ ሃይማኖት

(ትሃመ ፱፩)

የቀዳማይ ክፍል ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ

በቦሌ ጥጎተ ብርሃን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን

ሰንበት ትምህርት ቤት

፲፱፻፩ ዓ.ም.

# ማውጫ

ትምህርተ ሃይማኖት .......... 1
(ትሃመ ፱፩) .......... 1
የቀዳማይ ክፍል ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ .......... 1
በቦሌ ኆኀተ ብርሃን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን .......... 1
ሰንበት ትምህርት ቤት .......... 1
፳፱፩ ዓ.ም.ማውጫ .......... 1
ማውጫ .......... 2

ምዕራፍ አንድ .......... 3
የትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ .......... 3
፩፦፩ የሃይማኖት ትርጉም - ሃይማኖት ምንድር ነው? .......... 3
ዕለተ ሰኑይ (ሰኞ ዕለት) .......... 19
3. ዕለተ ሠሉስ (ማክሰኞ ዕለት) .......... 20
4. ዕለተ ረቡዕ (ረቡዕ ዕለት) .......... 20
5. ዕለተ ኀሙስ (ኀሙስ ዕለት) .......... 20
6. ዕለተ ዓርብ (ዓርብ ዕለት) .......... 20

# ምዕራፍ አንድ

## የትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ

### ፩፡-፩የሃይማኖት ትርጉም - ሃይማኖት ምንድር ነው?

**ሃይማኖት** የቃሉን ፍቺ ስንመለከት አምነ = አመነ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ማመን፣ መታመን ማለት ነው።

**ማመን (እምነት)፡-** የተማሩትን፣ የሰሙትን እውነት ነው ብሎ በልብ መቀበል ሲሆን **መታመን (ተአምኖ)** ማለት ደግሞ እውነት ነው ብለው የተቀበሉትን አውነትነቱ እንዲረጋገጥ በሰው ፊት መመሥከርና በተግባር መግለጥ ነው። ሐዋርው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ እንዳለ፡-

> ‹‹ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው። ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሠክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን ለይቶ እንዳስነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህ››
>
> (ሮሜ ፲፥፱-፲)

ስለዚህ ስለፈጣሪ የሚነገረውን በልብ አምኖ መቀበል፣ ያመኑትንም በአንደበት መመሥከርና በተግባር መግለጥ ተጠቃሎ ሃይማኖት ይባላል።
በተጨማሪም የሚከተሉት ነጥቦች የሃይማኖትን ምንነት የሚገልጡ የሚያብራሩ ናቸው።

**ሀ) ሃይማኖት መሠረት ነው፡-**

> ‹‹ አሚንሰ መሠረት ይእቲ ወካልኣኒሃ ሕንጻ ወንድቅ እሙንቱ - እምነት መሠረት ናት ሌሎቹ ግን ሕንፃና ግንብ ናቸው››
>
> (ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሕንፃና በግንብ መስሎ የተናገራቸውና ሌሎቹ ብሎ የጠቀሳቸው ምግባርንና ትሩፋትን ነው። እምነት/ሃይማኖት ግን የእነዚህ መሠረት ናት። ይህም ሕንፃን ከመገንባት በፊት ሀልዎተ ፈጣሪን (የፈጣሪን መኖር) ማመንና በሚሠሩት ምግባር ትሩፋት የሚያምኑት ፈጣሪ የማያልፍ የማይጠፋ ዋጋን እንደሚሰጥ በእምነት መቀበል ይቀድማል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ እንዳለ፡-

> ‹‹ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው አስቀድሞ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጣቸው ሊያምን ይገባዋል።››
>
> (ዕብ ፲፩፥፮)

በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፮ ቁጥር ፲፮ ላይ ዐለት በተባለው በቅዱስ ጴጥሮስ እምነትና ምሥክርነት ማመን (ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ አምላክ መሆኑን

ማመን) የሁሉ መሠረት እንደሆነና ከዚህ በኋላ ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን በፈተና ጸንቶ ለዋጋ የሚያበቃ ሥራን መሥራት እንደሚገባ እንደሚከተለው አብራርቷል፡፡

> ‹‹ መሠረቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ላይ በወርቅና በብር በከበረ ድንጋይና በእንጨት በሣርና በአገዳ የሚያንጽ ቢኖርም የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ እሳትም በፈተነው ጊዜ ቀኑ ይገልጠዋል፤ የእያንዳንዱንም ሥራ እሳት ይፈትነዋል፡፡ ሥራው ጸንቶ የተገኘለት ሰው ዋጋውን የሚቀበል እርሱ ነው፡፡ ሥራው የተቃጠለበት ግን ዋጋውን ያጣል፡፡››
>
> (፩ኛ ቆሮ ፫፥፲፩-፲፭)

**ለ) ሃይማኖት ከእውቀት በላይ ነው**

ሰው በስሜት ሕዋሳቱ መርምሮ ያውቃል፡፡

## ፩-፫. የሃይማኖት አስፈላጊነት (በነፍስ በሥጋ)

ሃይማኖት ለሥጋም ለነፍስም አያሌ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡ ሁሉን ዘርዝሮ መፈጸም ባይቻልም የሚከተሉትን ዐበይት ጥቅሞች እንመለከታለን፡፡

### ሀ) ሃይማኖት ለሥጋዊ ሐይወት የሚሰጠው ጥቅም

### ፩ኛ. ሰላምን ያሰጣል

ሰላም ፍጹም የሆነ ውስጣዊ እረፍት ነው፡፡ ሰው በሃይማኖት ከኖረ ውስጣዊ ሰላሙን የሚያደፈርሱ ፈተናዎችን፣ አእምሮን የሚያልፉ ጭንቀቶችን ሁሉ በተአምኖ እግዚአብሔር ድል ስለሚያደርግ እረፍት የሚያሰጡ ኃጢአቶችንም በንስሐ ስለሚያስወግድ ዘወትር ሰላም አይለየውም፡፡ ይህ ደግሞ ለሥጋዊ ሕይወት መሠረታዊ ጥቅም አለው፡፡ ምክንያቱም ሰው በሥጋዊ ሕይወቱ ውጤታማ የሚሆነው ተማሪው ተምሮ መመረቅ፣ ነጋዴው ነግዶ ማትረፍ፣ ሙያተኛው ሠርቶ ራስንና ወገንን መደገፈ የሚቻለው እያንዳንዱ ውስጣዊ ሰላም ሲኖረው ነው፡፡ ሰላም የሌለው ሰው ግን ዘወትር ከራሱ ጋር ስለሚጋጭና ስለሚጣላ በማንኛውም ቦታ የተሰጠውን ኃላፊነት የሚወጣበት አቅም አይኖረውም፡፡
በሃይማኖት የሚኖር ሰው ሁሉን ማድረግ በሚቻለው በእግዚአብሔር በመደገፍ እውነተኛውን ሰላም ያገኛል፤ ልቡናውም ከጭንቀት ይጠበቃል፡፡ የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ይህንን ያስረዳሉ፡፡

> ‹‹ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜንም እስጣችኋላሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም፤ ልባችሁ አይደንግጥ አትፍሩም፡፡››
>
> [ዮሐ ፲፬፥፳፯]
>
> ‹‹ሁሉ የሚገኝባት ከልቡናና ከአሳብ ሁሉ በላይ የምትሆን የእግዚአብሔር ሰላም በኢየሱስ ክርስቶስ ልባችሁንና አሳባችሁን ታጽናው››
>
> [ፊል ፬፥፯]
>
> ‹‹በአንተ ላይ ታምናለችና በአንተ የምትደገፍ ነፍስን ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ››
>
> [ኢሳ ፳፮፥፫]

### ፪ኛ. መንፈሰ ጠንካራ ያደርጋል

ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ብዙ ተግባራት አሉት፡፡ከነዚህ ውስጥ እጅግ አድካሚ፣ እልህ አስጨራሽና ተስፋ አስቆራጭ የሆኑ መኖራቸው አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በሃይማኖት (በአሚነ እግዚአብሔር) የማይኖረው የሚታመነው ስለሌለው ተመርሮና ተስፋ ቆርጦ ሲተዋቸው በሃይማኖት የሚኖረው ግን «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» ብሎ በጠንካራ መንፈስ ሊወጣቸው ይቻለዋል፡፡ (ፊል ፬ ፥፲፫ ) ፡፡

የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ ከተላኩት ጉበኞች (ሰላዮች) የምንረዳውም ይህንኑ ነው፡፡ የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ በተላኩበት ጊዜ ፲፪ቱም ሰላዮች ምድሪቱ መልካም እንደሆነች ነገር ግን በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ኃያላን እጅግም ግዙፋን መሆናቸውን አይተዋል፡፡ ነገር ግን ፲ሩ ተአምኖ እግዚአ የጎደላቸው በመሆናቸው ተስፋ ቆርጠዋል፤ ፈተናውን ማለፋ ተስኗቸዋል፡፡ ሕዝቡንም በአመጡት ወሬ አሸብረዋል፡፡ ሕዝቡም የተስፋይቱን ምድር መውረስ ዓላማ አድርገው ብዙውን መከራ ተቀብለው በበረሃ አልፈው መጥተው ጥቂት መንገድ ሲቀራቸው «ኑ አለቃ ሾመን ወደ ግብጽ እንመለስ» የሚሉ

ሆነዋል። (ዘኍ ፲፬፥፬)። በእምነት ጽኑአን የነበሩት መንፈሰ ጠንካሮቹ ኢያሱና ካሌብ ግን «አይደለም ማሸነፉን እንችላለንና እንውጣ እንውረሳት» (ዘኍ ፲፫፥፴) ብለዋል።
በሃይማኖት የሚኖር ሰው ኃያሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑን ስለሚያምን ምንም ያህል ከባድ ፈተና ቢገጥመው ያጋጠመውን ፈተና እግዝፎ፣ ራሱን እንደ አንበጣ አሳንሶ አይመለከትም። (ዘኍ ፲፫፥፴፪) ከዚህ ይልቅ ፈተናውን ከማለፍ በኋላ ያለውን መልካም ነገር ስለሚያይ በፈተናው ውስጥ በብርቱ መንፈስ ሆኖ ያልፋል።

### ፫ኛ. ታማኝና ተወዳጅ ያደርጋል

በሃይማኖት የሚኖር መንፈሳዊ ሰው በሁሉ ነገር በሰው ሁሉ ፊት ይታመናል። ይህም በሁሉ ፊት ሞገስን እንዲያገኝ ስለሚያደርገው የሚቃወመው፣ ጉዳት ሊያደርስበት የሚፈልግ፣ የሚጠላው ሰው አይኖርም። ሰይጣን በቅንዓት አንዳንዶችን በክፋ ቢያስነሳበት እንኳ በፈተናው ስለሚጸና ፈተናውን ሲያልፋ ከፊት ይልቅ የሚበልጥ ታማኝነትንና ተወዳጅነት ያተርፋል። ይህንንም ከቅዱስ ዩሴፍ ሕይወት መማር ይቻላል። ለባርነት በተሸጠበት በባዕድ ሀገር ሀገርን እስከ መምራት ድረስ ታማኝነትንና ተወዳጅነትን ያገኘው ፈሪሃ እግዚአብሔር፣ አሚነ እግዚአብሔር ስለነበረው ነው። (ዘፍ ፴፱)።

### ፬ኛ. ትዕግስተኛ ያደርጋል

በሃይማኖት የሚኖር ሰው ሁሉ በፈቃደ እግዚአብሔር የሚከናወን መሆኑን ስለሚያምን በሥጋዊ ሕይወቱ ድንገተኛ ችግሮች ቢያጋጥሙት (ሀብት ንብረት ቢወድም፣ አካል ቢጎድል፣ . . .) ይታገሳል እንጂ መድኃኒት ጠጥቼ፣ ገደል ገብቼ ልሙት አይልም። ይልቁንም እንደ ጻድቁ ኢዮብ «እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔርም ነሣ፣ እግዚአብሔርም እንደፈቀደ ሆነ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን» እያለ እግዚአብሔርን ከማመስገን አይቦዝንም። (ኢዮ ፩፥፳፯) ።
በሌላም መልኩ በሃይማኖት የሚኖር ሰው ከሰዎች የሚሰነዘሩበትን ፈተናዎች ሁሉ በትዕግስት ይቋቋማል። ክፋውን ሁሉ በመልካም (በትዕግስት) ያሸንፋል እንጂ በክፋ ስለማይሸነፍ ለበቀልም ስለማይነሣሣ ወንጀል ፈጽሞ በሥጋው ላይ መከራን አይመጣም። (ሮሜ ፲፪፥፳፩) ።

### ፭ኛ. በረከተ ሥጋን ያሳጣል

በሃይማኖት የሚኖር ሰው እግዚአብሔርን በማመኑ በሥጋዊ ሕይወቱ ያሉት ነገሮች ሁሉ የተባረኩ ይሆናሉ። በተቀደሰ ጋብቻ ኖሮ የተባረከ ልጅ ይወለዳል፤ አሥራቱን አውጥቶ ሀብቱ ንብረቱ የተባረከ ይሆናል፤ ጥቂቱ ይበዛለታል ጉዶሎው ይሞላለታል።

- አብርሃም በቅዱስ ጋብቻ ኑሮ ዘሩ የተባረከ እንደሆነ (ዕብ ፲፯፣፳)
- የሰራፕታዋ ሴት በእግዚአብሔር አምና የነቢዩ የኤልያስን ቃል ስምታ እንደተባለችው ስላደረገች ቤቷ በበረከት እንደተሞላ ( ፩ኛ ነገ ፲፯፣ ፲ ፲፯)
- የዶኪማስ የሠርጉ ቤት በጌታ የተአምራት ሥራ፣ በእመቤታችን ምልጃ በበረከት እንደተጎበኘ (ዮሐ ፪፣ ፲፯)

### ፮ኛ. ድህነተ ሥጋን ያሠጣል

ሰው በተለያየ ምክንያት የሥጋ ሕመም (ደዌ) ሊያገኘው ይችላል። በሃይማኖት የሚኖር ከሆነ ግን በእምነቱ ብቻ ፍጹም ፈውስን ሊያገኝ ይችላል። ሃይማኖት ለደዌ ነፋስ (ኃጢአት) በንስሐ ፈውስን እንደምትሰጥ ለደዌ ሥጋም በተአምር ፈውስን ታስገኛለች። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ

ስብከቱ ብዙዎችን በእምነታቸው ምክንያት ከተለያየ ደዌ ሥጋ እንደፈወሳቸው በወንጌል ተጽፎ እናነባለን፡፡ (ማር ፱፥፳፫፤ ሉቃ ፲፯፥፲፱፤ ማቴ ፱፥፳፪፤ ማቴ ፰፥፲፫)

### ፯ኛ. ከመከራ ሥጋ ያድናል ይሰውራል

በሃይማኖት የሚኖር ሰው በሥጋ መከራ ቢደርስበት የሚያምነው አምላኩ በክንፈ ረድኤቱ ከመከራ ይሠውረዋል፡፡ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ክብርን፣ ዐስበ ሰማዕታትን (የሰማዕታትን ዋጋ) ያገኝ ዘንድ ፈቅዶ ካልተወው በቀር እሳቱን፣ ሰይፉን ስለቱን ሁሉ ያርቅለታል፡፡

- ዳንኤልን ከተራቡ አናብስት አፉ እንዳዳነው (ዳን ፮፥፲-፳፫)
- ሠለስቱ ደቂቅን ከሚነድ እሳት እንደታደጋቸው (ዳን ፫፥፲፱-፴)
- ሶስናን በድንጋይ ተወግራ በእሳት ተቃጥላ ከመሞት እንዳዳናት (ዳን ፲፫፥፴)

## ለ) ሃይማኖት ለነፋስ የሚሰጠው ጥቅም

ሃይማኖት ለሥጋ ያለውን ጥቅም ስናነሳ ሥጋን የሚጠቅሙ ነገሮች ነፍስንም የሚጠቀሙ፣ ሥጋን የሚጎዱም ነገሮች ነፋስን የሚጎዱ መሆናቸው ሊስተዋል ይገባል፡፡ ነፋስ ያለሥጋ አትቆምምና፡፡ በሥጋዊ ሕይወቱ ውስጣዊ ደስታ የሌለው ሰላም የተሞላበትና ስኬታማ ኑሮን መምራት ያልቻለ ሰው ስለነፋሱ ደኅነት የማይጨነቅ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ግድ የለሽ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን በሃይማኖት የሚኖር ሰው በነፋሱ የሚከተሉትን ጥቅሞች ያገኛል፡፡

### ፩ኛ. በነፋሱ ድኅነትን ይገኛል

ሰው በነፋሱ ድኅነት አገኘ የምንለው ከዘላለም ፍርድ አምልጦ ገነት መንግስተ ሰማያትን መውረስ ሲችል ነው፡፡ ለዚህ ድህነተ ነፋስ ለመብቃትም ርቱዕ ሃይማኖትን መያዝ በጐ ምግባር መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ያለ ሃይማኖት ድህነተ ነፋስን ማግኘት የለም፡፡

«በእርሱ ያመነ አይፈረድበትም፤ በእርሱ ያላመነ ግን ፈጽሞ ተፈርዶበታል»

(ዮሐ ፫፥፲፰)

እምነት ወደ ድህነት ለመድረስ ለሚደረገው የሕይወት ሙሉ ጉዞ የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ሮማዊውን የእስር ቤቱን ዘብኛ እንዲህ ያሉት፡-

«በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ››

(ሐዋ ፲፮፥፴፩)

### ፪ኛ. በነፋሱ ዘላለማዊ ዋጋን ያገኛል

ሰው ሃይማኖትን ጠብቆ በምግባር ጸንቶ በነፋሱ ድኅነትን ሲያገኝ ነፋሱ የማይጠፋ ዘላለማዊ ሽልማትን ትቀዳጃለች፡፡ ይህም የነፋስ ሰማያዊ ዋጋዋ ነው፡፡ ይህ ዋጋ ፡-

- ***የሕይወት አክሊል ነው***

«መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ፣ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ፡፡ እንግዲህ የጽድቅ አክሊል ይቆየኛል ይሁንንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር በዚያ ቀን ለእኔ ያስረክባል፡፡ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም፡፡»

(፪ጢሞ ፬፥፯-፰)

- ***የክርስቶስ መለኮቲዊ ክብር ተካፋዮች መሆን ነው ይህም ክርስቶስን መምሳል ነው***

«እኛስ ሀገራችን በሰማይ ያለችው ናት፤ ከዚያም እርሱን ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን። እርሱም እንደ ከሀሊነቱ ረዳትነት መጠን የተዋረዳውን ሥጋችንን የሚያድሰው ክቡር ሥጋውንም እንዲመስል የሚያደርገው፣ የሚያስመስለውም ሁሉም የሚገዛለት ነው»

(ፊል ፫፥፳ እና ፳፩)

- ***የእግዚአብሔርን መንግሰት መውረስ ነው***

ሰው በቀናው ሃይማኖቱና በበጐ ምግባሩ ሀዘን፣ ጩኸት፣ ሕማም፣ መከራ፣ ሞት የሌለባትን የእግዚአብሔር ክብር የሞላባትን መንግስቱን ይወርሳል። (*ራዕ* ፳፩፥፩-፳፯)

# ምዕራፍ ሁለት

## ህልዋተ ፈጣሪ - የፈጣሪ መኖር

በዚህ ምዕራፍ የፈጣሪን መኖር ማመን የሃይማኖት መሠረት ስለመሆኑ፣ የፈጣሪን መኖር ስለሚያስረዱ አስረጂዎች፤ ስለ እግዚአብሔር ባሕርያትና ስሞች እንመለከታለን

### ፪ ፪ *የሃይማኖት መሠረት - ፈጣሪን ማመን*

*ሃይማኖት ማለት የ፳፪ቱ ሥነ-ፍጥረት አስገኚ፣ የሚታየውና የማይታየው ዓለም ሠራዒ መጋቢ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችል ረቂቅ ምሉዕ ስፉሕ፣ ሕያ ባሕርይ የሆነ እግዚአብሔር ነው ብሎ ማመን ነው። የዚህ እምነት መሠረቱ የፈጣሪ መኖር (ህልዎተ ፈጣሪ) ነው። የፈጣሪ ‹‹መኖር›› ስንል ግን ለአኗኗሩ ጥንት ወይም ፍጻሜ አለው ማለት ሳይሆን ዘመኑ የማይለካ ከጥንት በፊት የነበረ ጥንት ከመጨረሻም በኋላ የሚኖር መጨረሻ ብለን ለመናገር መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ሃይማኖትን ያጸኑ ኦርቶዶክሳውያን አባቶች በጸሎተ ሃይማኖት እንዲህ ብለዋል፡፡*

> ‹‹ሁሉን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ሰማይንና ምድርን ፈጠረ የሚታየውንና የማይታየውን»
>
> (ሠለስቱ ምዕት)

በመሠረቱ ዓለም ያለ አስገኚ የተገኘ፣ ከተገኘም በኋላ ያለ መጋቢ በራሱ የሚኖር አይደለም። ሸክላ ያለ ሠሪ፣ ቡቃያ ያለመሬት፣ ልጅ ያለ እናት አባት እንደማይገኙ ሁሉ ዓለምም ያለ አስገኚ የተገኘ አይደለም። ለተፈጥሮው አስገኚ፣ ለኑሮው ሠራዒ መጋቢ፣ ለጉዞው መነሻና መድረሻ አለው እንጂ። ይህንንም በልቡና መርምረን በቃለ እግዚአብሔር ምስክርነት በእምነት እናውቃለን።

> «ዓለም በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ፣ የሚታየው ነገር ከማይታይ እንደሆነ በእምነት እናውቃለን››
>
> (ዕብ ፲፩፥፫)

ከዚህ ቀጥሎም የፈጣሪን መኖር የሚያስረዱ ነገሮችን እንመለከታልን

### ፪.፪ *የፈጣሪን መኖር የሚያስረዱ ነገሮች*

**ሀ) ሥነ-ፍጥረት**

የማይታይና የማይዳሰሰው አምላክ በሚታይና በሚዳሰሰው *ሥራው* (*ሥነ-ፍጥረት*) ራሱን ስለገለጠ *ሥነ* ፍጥረት ለፈጣሪ መኖር አንድ አስረጂ ነው
*ሥነ* ፍጥረት የፈጣሪን መኖር የሚያስረዳው በሁለት ወገን ነው።

፩ኛ. ከፍጥረታት መካከል በራሱ የተፈጠረ በራሱም ላይ ብቻውን ሙሉ ሥልጣን ያለው ፍጥረት አለመኖሩ። ይህም ለተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ አስገኚ ፈጣሪ በተፈጠረውም ፍጥረት ላይ ሥልጣን ያለው ኃይል እንዳለ ያሳየናል።

፪ኛ. በተፈጠረው ፍጥረት መካከል ያለው አብሮ የመኖር ስምምነት ለምሳሌ፦ ከእንስሳት የሚወጣውን የተቃጠለ አየር በመጠቀም በምትኩ ለእንስሳት በሕይወት መኖር የሚያስፈልገውን አየር ተክሎች መለገሳቸው፣ በዚህም በከባቢ አየር ውስጥ ለሁሉም በሕይወት ለመኖር የሚያስፈልጉ አየራት መጠናቸው ሳይዛባ የሚኖር መሆኑ በቂ አስረጂ ነው። ይህ የሚሆነው ግን እንስሶችም ተክሎችም ፈልገው አስበውበት የሚያደርጉት አለመሆኑ ፍጥረታትን ፈጥሮ በሥርዓት የሚያስተዳድር ኃይል (አምላክ) እንዳለ ያስረዳል።

ቅዱሳት መጽሐፍትም በሥነ-ፍጥረት የፈጣሪ ህልውና የሚታወቅ መሆኑን ይመሰክራሉ

«የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉና ጌትነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የፈጠረውን ፍጥረት በማሰብና በመመርመር ይታወቃል»

(ሮሜ ፩፥፳)

«አሁን ግን እንሶስችን ጠያቅ ያስተምሩህማል፣ የሰማይንም ወፎች ጠይቅ ይነግሩህማል፣ ለምድር ንገራት እርሷም ትተረጉምልሃለች፣ የባህርም ዓሳዎች ያስረዱሃለ፣ የእግዚአብሔር እጁ ይህን ሁሉ እንዳደረገ»

(ኢዮ ፲፪፥፯-፲)

«ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል»

(መዝ ፲፰፥፩)

ሌላው ግዕዛን (አእምሮ) የሌላቸው ወቅቶች ጊዜያቸውን ጠብቀው መፈራረቃቸው በዚህም ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ በምድር ላይ ምግበ ሥጋን አግኝቶ መኖር መቻሉ ወቅቶችን የሚያፈራርቅ ኃይል መኖሩን የሚያስረዳ ምስክር ነው።

«ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራን እየሠራ ከሰማይ ዝናምን፣ ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፣ ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም።»

(ሐዋ ፲፬፥፲፯)

## ለ) የሕሊና ምስክርነት

ሰው የተጻፈ ሕግ ባይኖረውም እንኳ መጽሐፍትንም ባያነብ አዋቂ ፍጥረት በመሆኑ መልካምና ክፉን በሕሊናው አመዛዝኖ መለየት ይቻለዋል።

«ሕግ የሌላቸው አሕዛብስ እንኳ ለራሳቸው ሕግ ያሠራሉ . . . በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ፣ ከሥራቸውም የተነሳ ይታወቃል ሕሊናቸውም ይመሰክርባቸዋል ይፈርድባቸዋልም»

(ሮሜ ፪፥፲፬ ና ፲፭)

ሰው የሁሉ ፈጣሪና ገዥ መኖሩን አምኖ ከሞት በኋላ ያለውንም ሕይወት ተስፋ አድርጐ ሲኖር በሕሊናው ፍጹም ሰለምን ያገኛል። በእንዳሩ ደግሞ እግዚአብሔርን ቅር የሚያሰኝ ሥራ ሲሠራ (ሲገድል፣ሲሰርቅን . . .) ሠሪው የሃይማኖት ሕግ ባይኖረውም እንኳ የተፈጥሮ ዳኛ ሕሊናው ስለሚፈርድበት በጭንቀት ይኖራል። አይሁድን የጨፈጨፈና በኢየሩሳሌም ላይ ትልቅ በደል ያደረሰ አሕዛባዊው አንጥያኮስ እንዲህ እንዳለ፦

‹‹

ይህም ማለት ሰው ሁሉ በሕሊናው አንድ ቅንና እውነተኛ ፈራጅ መኖሩን ያውቃል ማለት ነው።

## ሐ) እግዚአብሔር ከሰው ጋር ባደረገው ንግግር

እግዘአብሔር ከሰው ጋር በራዕይ በሕልምና በገሀድ ቃል በቃል ያደረገው ንግግር ህልውናውን ያረጋግጣል።

«እግዘአብሔርም ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር»

(ዘፀ ፴፫፥፲፩)

የሙሴ እህት ማርያምንና አሮንንም በዐምደ ደመና ተገልጦ እንዳነጋገራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። (ዘኁ ፲፪፥፳-፲)

**መ) የሰው ልጅ ሃይማኖታዊ ዝንባሌ**

ከጥንት ጀምሮ ያለውን የሰው ልጅ ታሪክ ስንመለከት ወይ በእግዚአብሔር ሲያምን አልያም የእግዚአብሔር የእጁ ሥራዎች በሆኑ በፀሐይ፣በጨረቃ . . . ወ.ዘ.ተ. ሲያምን ወይም ደግሞ በራሱ በእጁ አለዝቦ፣ ጠርቦ ቀርጾ ያዘጋጃቸውን ጣዖታቱን ሲያመልክ መኖሩን እንገነዘባለን። ይህም የሰው ልጅ ለመኖር ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ የተፈጥሮ ፍላጎቶች ባልተለየ ሁኔታ የእምነት ዝንባሌና ስሜት እንዳለው ያሳያል። ሰው እንዲህ በተፈጥሮው በራሱ ምሉዕ አለመሆኑ፣ የማይሸነፍ ብርቱ ረዳት መፈለጉ ሁሉን ቻይ፣ ጸባዖት (አሸናፊ) አምላክ መኖሩን ያሳያል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን የሰውን የማመን ዝንባሌ ተጠቅሞ በአቴና ከተማ «ለማይታወቅ አምላክ» የሚል ጽሑፍን መነሻ አድርጎ በአቴና ከሚኖሩት አንዳንዶችን ወደ አምልኮ እግዚአብሔር አምጥቷቸዋል። (ሐዋ ፲፯፥፳፪-፴፬)

ከላይ የተዘረዘሩትን አስረጂዎች ተገንዝቦ ፈጣሪ እንዳለ ማወቅ አእምሮ ለተሰጠው ለሰው ልጁ ስውር አይደለም። ሆኖም ይህን አለማስተዋልና የእግዚአብሔርን ህልውና መጠራጠር ግን ስንፋና ነው። የእግዚአብሔር ቃልም ይህንኑ ያስረዳል።

> «ሰነፋ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል»
>
> (መዝ ፲፫፥፩)
>
> ‹‹እግዚአብሔርን የማወቅ ጉድለት በልቦናቸው ያለባቸው ሰዎች ሁሉ በእውነት ከንቱ ናቸውና፤ በሚታዩ መልካም ነገሮች ያለውን ያውቁ ዘንድ ተሳናቸው፤ ሥራውንም እያዩ ሠሪውን አላወቁትም።››
>
> (ጥበ ፲፫፥፩)

## ፪ ፫ የአምላክ ስሞች (አስማተ አምላክ)

ሀለወተ ፈጣሪን ተረድቶ በሃይማኖት የሚኖር ሰው የሚያምነውን አምላኩን እሱነቱንና ስሙን አእምሮው በሚፈቅድለት መጠንና ፈጣሪውም እሱነቱን በአስታወቀለት መጠን ሊያውቀው ሊረዳው ይገባል። የእግዚአብሔር ባሕርዩንና ግብሩን የሚገልጸው ስሙ ለሰው ልጅ የታወቀለት በራሱ በእግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር ከሙሴ በፊት ለነበሩት አበው እሱነቱን ሲገልጥላቸው ስሙ «ኤልሻዳይ» እንደሆነ በመንገር እንጂ ስሙ እግዚአብሔር መሆኑን አልገለጠላቸውም ነበር። የዚህም ስም ትርጉም ‹‹ሁሉን ቻይ›› ማለት ነው። ለሰው ልጅ በቅድሚያ ስለ እግዚአብሔር ግልጥ የሆነው ከሀሊነቱ (ሁሉን ቻይ መሆኑ) ነውና። ከዚህ በኋላ ግን በሊቀ ነቢያት ሙሴ ስሙ ማን እንደሆነ ተጠይቆ ሲመልስ ‹‹ያለና የሚኖር›› ደግመኛም ‹‹የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ›› የሚለው ለዘለዓለም ስሙ እንደሆነ ገልጧል። (ዘፀ ፫፥፲፴)። ከዚህ በመቀጠልም በእስራኤላውያን ቋንቋ ‹‹ይሆዋ›› ወይም ‹‹ያህዌ›› በሚል ስም አንደሚጠራ ግልጽ አድርጓል። ይህም ወደ ግዕዝ ሲመለስ ‹‹እግዚአብሔር›› በሚል ቃል ተተክቷል።

> ‹‹እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ለአብርሃምም ለይስሐቅም በያዕቆብም ሁሉን እንደሚችል (ኤልሻዳይ) አምላክ ተገለጥሁ። ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር አልታወቀላቸውም ነበር።›› እንዲል።
>
> (ዘፀ ፮፥፫)

ለነቢዩ ለኢሳይያስም ይህንን ስሙን ገልጾለታል።

> ‹‹እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ፣ ስሜ ይህ ነው፣ ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም››
>
> (ኢሳ ፵፪፥፰)

ይህም እግዚአብሔር የሚለው ስም የሁሉን ፈጣሪ አስገኚና መጋቢ ከነባሕርዩና ግብሩ እሱነቱን በጠቅላላ የሚገልጽ ስም በመሆኑ ክቡር ነው። እግዚአብሔር አምላካዊ ግብሩን በሚገልጡ ስያሜዎች ‹‹አምላክ፣ ፈጣሪ፣ ጌታ ከሃሊ፣ መጋቢ፣ አዳኝ፣ . . . ወዘተ›› ተብሎ ይጠራል። አምላካዊ

ባሕርዩንም በሚገልጡ ‹‹ሕያው፣ ዘላለማዊ፣ ያለና የሚኖር፣ መሐሪ፣ … ›› በሚሉ ስያሜዎች ይጠራል፡፡ እግዚአብሔር የሚለው ስያሜ ግን እርሱነቱን ከነባሕርይውና ግብሩ የሚገልጽ በመሆኑ ይህ ስም ለፈጣሪ የመጨረሻው (የመጠሪያ ስም) ነው፡፡ በዚህም ስም አምልኮታችንን እንፈጽማለን፡፡ ይህም ስለሆነ ከዐሥርቱ ሕግጋት አራት አንዱ ይህንን ቅዱስና ክቡር ስም በከንቱ መጥራትን ይከለክላል፡፡

> ‹‹የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ አምላክህ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና››
>
> (ዘጸ ፳፥፯)

‹‹ያሆዋ›› ወይም ‹‹ያህዌ›› የሚለው ስም በአይሁድ ዘንድ በዓመት ውስጥ በተወሰነ ጊዜ ያውም በሊቀ ካህናቱ ብቻ ከልሆነ በቀር በማንኛውም ጊዜ፣ በማንኛው ሰው በግልም ይሁን በማህበር ጸሎት ላይ አይነሣም፡፡ በዚህ ፋንታ ግን ‹‹ኤሎሄ››/‹‹ኤሎሂም›› (አምላክ/አማላኬ)፣ ‹‹አዶን››/‹‹አዶኒ››/‹‹አዶናይ›› (ጌታ/ጌታዬ) ፣ ‹‹ኢሊዮን››/‹‹ኤል›› (ልዐል) በሚል የተጸውዖ ስም እግዚአብሔርን ይጠሩታል፡፡ እነዚህንም የተጸውዖ ስሞች እግዚአብሔር/ያህዌ ከሚለው ጋር እያጣመሩ መጥራት የተለመደ ነው፡፡

> ‹‹ጌታ እግዚአብሔር›› (ሕዝ ፪፥፬)
>
> ‹‹ልዑል እግዚአብሔር›› (ዘፍ ፲፬፥፲፰)
>
> ‹‹እግዚአብሔር አምላክ››

በዚህም መሠረት ለልጅም ይሁን ለድርጅት ስይሜ ሲያወጡ ይህን ቅዱስ ስም በቀጥታ መጠቀም ተገቢ እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባል፡፡

## ፪-፬ *የእግዚአብሔር ባሕርያት (ባሕርያቱ ለእግዚአብሔር)*

በዚህ ርዕስ ሥር የምንመለከተው እግዚአብሔር ስለ ባሕርይው የሰው ልጅ እንዲያውቀው በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል ከተገለጠው ጥቂቱን ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ግን ሰው የፈጣሪውን ባሕርይ መርምሮ የሚደርስበት አእምሮ የሚገልጽበትም ቋንቋ አይኖረውም፡፡
ከዚህ በታች የምንመለከታቸውን የእግዚአብሔር ባሕርያት ናቸው ስንል ከሌላ ከማንም ያለገኛቸው ማንም ደግሞ ከእርሱ ሊወስዳቸው የማይቻለው የራሱ ገንዘቦቹ ናቸው ማለታችን ነው፡፡ ከዚህ ከባሕርይ ገንዘቡም ለፍጡር ቢሰጥ እንዲት ሻማ ብርሃንን ለሌሎች ሻማዎች ብትሰጥ የራሷ ብርሃን እንደማያልቅባት የእርሱም ገንዘቡ የማያልቅበት ነው፡፡

እግዚአብሔር በባሕርዩ፡-

**፩ኛ- ዘላለማዊ (ሕያው) ነው**

እግዚአብሔር የሌለበት ጊዜ የለም፡፡ ፍጥረታትን ከመፍጠሩ በፊት በባሕርዩ የኖረ ነው፡፡ የሚታዩትና የማይታዩት ፍጥረታት ከእርሱ ተገኙ እንጂ እርሱን የፈጠረ/ያስገኘ ማስገኘትም የሚቻለው ሌላ ኃይል የለም፡፡ እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት ነበር፡፡ የጊዜና የዘመን ፈጣሪና ባለቤት እንጂ ዕለትና ጊዜ እርሱን አይቀድሙትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ስለዚህ ምስክር ነው

> *‹‹ተራሮች ሳይወለዱ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ መቼም መች አንተ ነህ››*
>
> (መዝ ፹፱፥፪)

እግዚአብሔር በራሱ የነበረ ያለና የሚኖር ስለሆነ በጊዜ አይወስንም ጊዜም እርሱን አይወስነውም፡፡ በባህርይውም እርጅናና መለወጥ የለበትም፡፡

> *‹‹አቤቱ አንተ አስቀድመህ ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው፡፡ እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ፡፡ ሁሉ እንደ ልብስ ያረጃል እንደ መጎናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፣ ይለወጡማል፡፡ አንተ ግን ያው አንተ ነህ ዓመትህም ከፋ አይልቅም››*
>
> (መዝ ፻፩፥፳፭-፳፯)

ከእግዚአብሔር በፊት የነበረ መጀመሪያ አልነበረም፡፡ ከእርሱም በኋላ የሚኖር መጨረሻ አይኖርም፡፡ እርሱ መጀመሪያና መጨረሻ ፊተኛና ኋለኛ ነው፡፡

> ‹‹የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር የሚቤዥም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እኔ ፊተኛ ነኝ እኔ ኋለኛ ነኝ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም፡፡››
>
> (ኢሳ ፵፬፥፮)

በተጨማሪም የሚከተሉት ጥቅሶች የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት ይገልጣሉ፡፡ (ራዕ ፩፥፲፰፤ ፩ኛ ጢሞ ፩፥፲፯፤ ዘጸ ፫፥፲፬)

**፪ኛ. ምሉዕ ነው**

እግዚአብሔር የሌለበት/የማይኖርበት ቦታ የለም፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው በጊዜ እንደማይወሰን ሁሉ በቦታም አይወሰንም፤ በሁሉም ቦት እርሱ አለ፡፡ እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ሙሉ እንደሆነ ልበ አምላክ ዳዊት እንደዚህ ገልጾታል፡፡

> ‹‹ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ፡፡ ወደ ጥልቁም ብወርድ አንተ በዚያ አለህ፡፡ እንደ ንስር ክንፍን ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር በዚያ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ታኖረኛለች››
>
> (መዝ ፻፴፰፥፯-፲)

በነቢዩ ኤርምያስም አድሮ እግዚአብሔር ምሉዓ ባሕርይነቱን ገልጧል፡፡

> ‹‹እኔ ቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ ሩቅ አምላክ አይደለሁም ይለል እግዚአብሔር ሰው በሰውር ቦታ ቢሸሽግ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን ይላል እግዚአብሔር››
>
> (ኤር ፳፫፥፳፫ እና ፳፬)

በተጨማሪም የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተመልካት፡፡ (ኢሳ ፷፮፥፩፤ መዝ ፻፪፥፲፱፣ ኢሳ ፮፥፫)

**፫ኛ. ሁሉን ማድረግ የሚቻለው (ከሀሌ ኵሉ) ነው**

እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚቻለው የሚሳነው የሌላ ነው፡፡ የተፈጠረ ፋጥረት ሁሉ የሚታየውም የማይታየውም ዓለም የችሎታው ውጤት ነው፡፡ ከተፈጠረው ፍጥረት እንዳች ስንኳ ያለ እርሱ የሆነ የለምና፡፡ (ዮሐ ፩፥፫)

እግዚአብሔር ሁሉን ያለአማካሪና ረዳት ያስገኘ ስለሆነም ሁሉ በእጁ የተያዘ ነው፣ ሁሉም በሥልጣኑ ሥር ነው፣ ሁሉን የመወሰን ሥልጣን ያለውም እርሱ ብቻ ነው፡፡ (ኢሳ ፵፥፲፪-፲፯፤ ፵፫፥፲፫፤ ፵፬፥፯)

እርሱ ራሱ እግዚአብሔርም ከሣራ ጋር በአደረገው የቃል በቃል ንግግር ሁሉን ቻይነቱን ገልጧል፡፡

> ‹‹በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሰነው ነገር አለን››
>
> (ዘፍ ፲፰፥፲፬)

ጻድቁ ኢዮብም፡-

> ‹‹ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ የሚሳንህም እንደሌላ እወቅሁ›› ብሏል፡፡
>
> (ኢዮ ፵፪፥፪)

ተጨማሪ ጥቅሶች፡- (ሉቃ ፲፰፥፳፯፤ ፩፥፴፯፤ መዝ ፻፴፬፥፮)

**፬ኛ. ቅዱስ ነው**

እግዚአብሔር በባሕርይው ልዩ ክቡር ነው፡፡ ርኩስት የማይሰማማውም ፍጹም ንጹሕ ነው፡፡ እግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ በሆነ በዚህ ቅድስናው ከማንም ጋር የማይነጻጸር የሚመስለውም የሌለ ነው፡፡

> ‹‹አቤቱ፡- በአማልክት መካከል አንተን የሚመስል ማነው? በቅዱሳንም ዘንድ እንደ አንተ የከበረ ማን ነው?›› እንዲል፡፡
>
> (ዘጸ ፲፭፥፲፩)

የሳሙኤል እናት ሐናም ይህን የእግዚአብሔርን ልዩ ቅድስና እንዲህ ገልጻዋለች፡፡

‹‹እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና››

(፩ኛ ሳሙ ፪÷፪)

ቅዱሳን መላእክትም ይህን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ቅድስና በመግለጥ ያለማቋረጥ እንዲህ እያሉ ያመሰግኑታል፡፡

‹‹ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ››

(ራዕ ፬÷፰)

ለዚህም ነው ቅዱስና ገናና ንጹሐ ባሕርይ እግዚአብሔር ሰውን በአርአያውና በምሳሌው በንጽሐ ባሕርይ ለክብር ስለፈጠረው የሰው ልጅ ከማንኛውም ርኩሰት ራሱን እንዲያነጻና በቅድስና እንዲኖር የታዘዘው፡፡

‹‹የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እንዲሁ እናንተም በአካሄዳችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፡፡››

(፩ኛ ጴጥ ፩÷፲፫)

ለግንዛቤ ያህል ከላይ ያሉትን ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት አነሳን እንጂ የእግዚአብሔር ባሕርያት እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት ግን አይደለም፡፡ አስቀድመን እንደተመለከትነው ፍጡር የፈጣሪውን ባሕርይ ሰፍሮ ቆጥሮ ዘርዝሮ የሚጨርሰው አይደለምና፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ሥነ - ፍጥረት

በዚህ ምዕራፍ የፍጥረታት መገኛና ባለቤት እግዚአብሔር ፍጥረታቱን የፈጠረበትን ዓላማ፣ እንዴት አድርጎ እንደፈጠራቸው (ፍጥረታቱን ያስገኘበትን ሁኔታ) እና መቼ እንደፈጠራቸው እንመለከታለን፡፡

## ፫ ፩ የሥነ-ፍጥረት ትርጉም

ሥነ ፍጥረት የሁለት ቃላት ጥምረት ነው፡፡ ‹‹ሥነ›› ያለው ‹‹ሠነየ›› መልካም ሆነ፣ አማረ፣ ተዋበ፣ በጀ ካለው የግዕዝ ግስ የተወሰደ ሲሆን መልካምነት፣ መበጀት፣ ውበት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሥነ ፍጥረት የሚለው ጣምራ ቃል በሁለት መልኩ ሊተረጎም ይችላል፡፡

፩ኛ. በተናባቢ ሲፈታ የፍጥረት መበጀት፣ የፍጥረት ማማር ማለት ይሆናል

፪ኛ. በቅጽል ሲፈታ (ሥነ የሚለው ቃል ፍጥረት ለሚለው ቃል ገላጭ ሲሆን) የበጀ ፍጥረት ያማረ ፍጥረት ማለት ይሆናል፡፡

እግዚአብሔር በከሀሊነቱ፣ ወሰን ድንበር በሌለው ዕውቀቱ የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ የበጀ በየሁኔታውም ብቁ ያማረ ፍጥረት ነውና ሥነ-ፍጥረት ተብሏል፡፡

‹‹እግዚአብሔርም የፈጠረውን ሁሉ እጅግ መለካም እንደሆነ አየ›› እንዲል፡፡

(ዘፍ ፩÷፴፩)

ከዚህም በተጨማሪ ሥነ-ፍጥረት ስንዐ ፍጥረት የፍጥረት መስማማት፣ የተሰማማ ፍጥረት ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ይህም የፍጥረት መገኛ የሆኑት ፬ቱ ባሕርያት (እሳትና ውኃ መሬትና ነፋስ) የማይስማሙ ሲሆኑ በእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ተስማምተው ስለሚኖሩ ነው፡፡ ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ ስለነዚህ ባሕርያት መስማማት እንዲህ ብሏል፡፡

‹‹ወአስተነዐዎሙ በበይናቲሆሙ እንዘ ዘዚአሁ ግእዘ ጠባይዒሆሙ - የየጠባያቸው ሥራ የተለያየ ሲሆን እርስ በእርሳቸው አስማምቷቸዋል››

(ዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን ፪)

## ፫ ፪ እግዚአብሔር ፋጥረታትን ለምን ፈጠረ?

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ከመፍጠሩ በፊት በቅድምና የነበረ ነው፡፡ በቅድሞናም ሲኖር ፍጥረትን ከመይጠሩ በፊት አንዳች የጎደለበት ነገር አልነበረም፡፡ በገዛ ባሕርያውም ይመሰገን ነበር፡፡ ይህም ፍጥረትን የፈጠረው የጎደለበት ኖሮ ፍጥረት እንዲሞላለት አለመሆኑን ያስረዳል

‹‹እምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ አኮ ዘተጸረዐ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ - መላእክትን ለምስጋና ከመፍጠሩም በፊት የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ምስጋናቸው የተቋረጠ አይደለም››

(፫፻ ቅዳሴ)

በመጽሐፈ ቀሌምንጦስም እንዲህ የሚል ተጽፏል፡፡

‹‹ይቅርታዬንና ክብሬን አስጠቸው ዘንድ ነው እንጂ ከነሱ እጠቀም ብዬ አልፈጠርኳቸውም››

(ቀሌምንጦስ)

ስለዚህ እግዚአብሔር ፍጥረታትን የፈጠረበት ዓላማ የሚከተሉት ናቸው

፩ኛ. ሰውና መላእክት ስሙን እንዲቀድሱ ክብሩን እንዲወርሱ ፈጥሯቸዋል፡፡ (ኢሳ ፵፫÷፯ ኤፌ ፩÷፲)

፪ኛ. የቀረውን ፍጥረት ለአንክሮ ለተዘክሮ (የሕልውናው መታወቂያ እንዲሆኑ) እና ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፋስ እንዲሆኑ ፈጥሯቸዋል፡፡ ለአንክሮ ለተዘክሮ ተፈጥረዋል ማለት ሥነ-ፍጥረትን በመመልከት፣ በመመራመር ሥራው እንዲደነቅ ህለውናው እንዲታወቅ ተፈጥረዋል ማለት ነው፡፡ ይኸውም ሸማን ስናይ ሸማኔ፣ ሸክላን ስናይ ሸክላ ሠሪ፣ ሕንፃን ስናይ ሐናጺ መኖሩን እንደምናውቅ ሁሉ በጥበብ የተፈጠረውንም ፍጥረት ስናይ ፈጣሪ እንዳላቸው ያስረዳልና ነው፡፡

‹‹የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ እርሱም የዘለዓለም ኃይሉና ጌትነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የፈጠረውን ፍጥረት በማሰብና በመመርመር ይታወቃል›› እንዳል፡፡

(ሮሜ ፩÷፳)

ለምግበ ሥጋ ተፈጥረዋል የተባሉትም አዝርእቱን፣ አትክልቱን፣ ፍራፍሬውን የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ለምግበ ነፍስ የተፈጠሩትም እንደ ስንዴውና፣ ወይኑ ያሉት ናቸው፡፡ የሕይወት (የነፋስ) ምግብ ሥጋውና ደሙ ይዘጋጅባቸዋልና፡፡

## ፫ ፪. *የስድስቱ ቀናት ፍጥረታት*

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር የተጠቀመባቸው ዕለታት ፯ ናቸው፡፡ እነርሱም እሑድ፣ ሰኞ ፣ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ኀሙስ፣ አርብና ቅዳሜ ናቸው፡፡ እነዚህን ዕለታት ቀድመን መዘርዘራችን በየዕለቱ በየተራ የተፈጠሩትን ለመመልከት ያስችለን ዘንድ ነው እንጂ ዕለታቱ ከፍጥረታቱ ቀድመው ተገኝተዋል ለማለት አይደለም፡፡ ዕለታቱ በእየአንዳንዳቸው ፍጥረታት ሲፈጠሩባቸው የተፈጠሩና የተገኙ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር በነዚህ ዕለታት ፍጥረታትን ያስገኘው ከሁለት ወገን ነው፡፡

፩ኛ. ***ካለመኖር ወደ መኖር /እምኃበ አልቦ ኀበ ቦ/ በማምጣት፡-*** በዚህ መልኩ የተፈጠሩት ፍጥረታት እግዚአብሔር በሥልጣኑ ቀድሞ ካልተገኘ ነገር ያስገኛቸው ናቸው፡፡

፪ኛ. ***ከተፈጠረው በመፍጠር /ግብር እም ግብር/፡-*** በዚህ መልኩ የተፈጠሩት ቁጥረታት ደግሞ አስቀድሞ ከተፈጠረ ነገር የተገኙ ናቸው፡፡

(መልመጃ ፳ቱን ሥነ ፍጥረት በሁለቱ ምድብ ሥር አስቀምጥ)

ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ወገኖች የፈጠራቸውን ፋጥረታት ያስገኘባቸው ደግሞ ሦስት መንገዶች አሉ

***፩ኛ. በማሰብ (በሐልዮ)***

እግዚአብሔር በዚህ መልኩ ከፍጥረታት ወገን ያስገኛቸውን የፈጠረው በቃሉ ሳይናገር በእጁም ሳይሠራ በሕሊናው በመፍቀድ ብቻ ነው፡፡

***፪ኛ.በመናገር (በነቢብ)***

እግዚአብሔር በዚህ መንገድ የፈጠራቸውን ፍጥረታት ያስገኘው ደግሞ ይሁን ብሎ በቃሉ አዝዞ ነው፡፡

***፫ኛ.በሥራ (በገቢር)***

እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ሁሉ በሥራ (በገቢር) ያስገኘው አደምን ብቻ ነው። እግዝእብሔር በመፍጠር ስልጣኑ «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» ብሎ ከምድር አፈር ሠርቶታል (አበጃጅቶታል)። (ዘፍ ፪፥፫) ይህንንም ልበ አምላክ ዳዊት እንዲህ ገልጾታል

«እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም»

(መዝ ፻፲፰፥፸፫)

## ፫ ፪ ፩ ዕለተ እሑድ

> እሑድ የሚለው ስም እሐደ አንድ አደረገ ከሰው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉምም አንድ፣ አንደኛ፣ መጀመሪያ ማለት ነው። የፍጥረት የመጀመሪያ ቀን ነውና።

እግዚአብሔር በዚህ ዕለት ራሱን ዕለቱንና ሌሎች ፍጥረታትን ፈጥሯል። እነዚህም ፍጥረታት፦

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ- እሳት | ፪ኛ- ነፋስ | ፫ኛ-ውኃ | ፬ኛ- መሬት |
| ፭ኛ- ጨለማ | ፮ኛ- ሰባቱ ሰማያት | ፯ኛ- መላእክት | ፰ኛ- ብርሃን ናቸው |

እግዚአብሔር ፍጥረታቱን ያስጋኘበት ሁኔታ እንደሚከተለው ነው።

***በቀደማይ ሰዓተ ሌሊት (ከሌሊቱ ፩ ሰዓት)፦***

በዚህ ሰዓት አራቱ ባሕርያት የተባሉትን መሬት፣ ውሀ፣እሳት፣ነፋስን እና ጨለማን እምኀበ አልቦ (ካለመኖር) አምጥቶ በሐልዮ በመፍቀድ ብቻ ፈጥሯቸዋል።

***ከሌሊቱ ፪ ሰዓት እስከ ሌሊቱ ፱ ሰዓት***

በነዚህ ሰዓታት ከእሳት ዋዕዩን (ማቃጠሉን፣ መቀቱን) ትቶ ብርሃኑን ነስቶ (ወስዶ) ሰባቱ ሰማያትን ፈጥሯል። የሰባቱ ሰማያት አፈጣጠርም እንደሚከተለው ነው።

፩ኛ- ከሌሊቱ ፪ ሰዓት ***መንበረ መንግስትን*** ፈጠረ። ከጽርሐ አርያም በታች ከሰማይ ውዱድ በላይ የምትገኝ ናት። መጠኗ የምንኖርባትን ዓለም የሚያህል፣ ከዳር እስከ ዳር የማይደርስ፣ አራት መዓዝን ቅርጽ ያላት ናት። በዚህች ሰማይ እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ በወደደው መልክ ይገለጥላቸዋል። (ኢሳ፮፥፩፤ ሕዝ ፩፥፳፮፤ ራዕ ፬፥፪)

፪ኛ- ከሌሊቱ ፫ ሰዓት ***ጽርሐ አርያምን*** ፈጠረ። ይህች ሰማይ ከሰማያት ሁሉ በላይ ናት። መጠኗም ይህን ያህላል፣ ድንበሯም እስከዚህ ድረስ ነው ብሎ ከፍጥረታት ወገን የሚያውቃት የለም።

፫ኛ- ከሌሊቱ ፬ ሰዓት ***ሰማይ ውዱድን*** ፈጠረ። ይህች ሰማይ ኪሩቤል የሚሸከሟት ለመንበረ መንግስት እንደ አዳራሽ ወለል የሆነችና መንበረ መንግስት እንደዙፋን የተዘረጋባት ናት።

፬ኛ- ከሌሊቱ ፭ ሰዓት ***ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን*** ፈጠረ። ሌላው ሰሟ ***መንግስተ ሰማያት*** ነው። ቀዳም ሳጥናኤል የተፈጠረባት፣ ክዶ ቢወጣ ለምዕመናን የተሰጠች ናት። በመካከሏ የእመቤታችን ምሳሌ የሆነ የብርሃን ታቦት (ታቦት ዘዶር) ይገኝባታል። (ራዕ ፲፩፥፲፱)

፭ኛ- ከሌሊቱ ፮ ሰዓት ***ኢዮርን*** ፈጠረ።

፮ኛ- ከሌሊቱ ፯ ሰዓት ***ራማን*** ፈጠረ።

፯ኛ- ከሌሊቱ ፰ ሰዓት ***ኤረርን*** ፈጠረ።

ኢዮር፣ ራማና ኤረር ዓለመ መላእክት (የመላእክት ከተሞች) ናቸው

***ከሌሊቱ ፱ ሰዓት እስከ ፲፪ ሰዓት***

በነዚህ ሰዓታት እግዚአብሔር መላእክትን በችሎታው ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጥሯል። በአንዳንድ መጻሕፍት (መዝ ፻፫፥፬፤ መቃ ፲፫፥፲፭፤ ድርሳነ ሚካኤል ዘኅዳር) ቅዱሳን መላእክት ከእሳትና ከነፋስ ተፈጥረዋል ተብሎ መጠቀሱ መላእክት እሳትና ነፋስን በግብር መምሰላቸውን ለማመልከት ነው። ይህም ማለት እሳት ረቂቅ ነው፣ መላእክትም ረቂቃን ናቸው፣ ነፋስ ፈጣን ነው መላእክትም ለተልእኮ ፈጣን ናቸው ለማለት ነው።

«ሶበስ ተፈጥሩ እምነፋስ ወነድ እሞቱ ወእማሰኑ ከማነ - ከነፋስና ከእሳትስ ተፈጥረው ቢሆን እንደ እኛ ታማሚ ሟች በሆኑ ነበር» እንዲል።

(አክሲማሮስ)

የተፈጠሩት መላእክት መቶ ነገድ ናቸው። አፈጣጠራቸውም እንደሚከተለው ነው።

፩ኛ. ከሌሊቱ ፱ ሰዓት በኢየሩሳሌም ሰማያዊ ያሉትን መላእክት ፈጥሯቸዋል

፪ኛ. ከሌሊቱ ፲ ሰዓት በኢዮር ያሉትን መላእክት ፈጥሯቸዋል

፫ኛ. ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት በራማ ያሉትን መላእክት ፈጥሯቸዋል

፬ኛ. ከሌሊቱ ፲፪ ሰዓት በኤረር ያሉትን መላእክት ፈጥራቸዋል።

ኢዮር ከላይ ወደታች አራት ከተማ ሲኖራት በእያንዳንዱ አሥር አሥር ነገደ መላእክትን አስፍሮባታል።

- በመጀመሪያው ከተማ ያሉትን አሥሩን ነገድ ***አጋዕዝት*** ብሎ ሰየማቻው፤ ሳጥናኤልን በእነሱ ላይ አለቃ አድርጎ ሾመው።
- በሁለተኛው ከተማ ያሉትን ***ኪሩቤል*** ብሎ ሰየማቸው፣ ኪሩብን አለቃቸው አደረገው።
- በሦስተኛው ከተማ ያሉትን ***ሱራፌል*** ብሎ ሰየማቸው፤ ሱራፊን አለቃቸው አደረገው።
- በአራተኛው ከተማ ያሉትን ***ኃይላት*** አላቸው። ሚካኤልን አለቃቸው አደረገው።

ራማ ከላይ ወደታች ሦስት ከተማ ሲኖራት በእያንዳንዳቸው አሥር አሥር ነገደ መለክትን አስፍሮባታል።

- በራማ በላይኛዋ (በመጀመሪያዋ) ከተማ ያሉትን ***አርባብ*** ብሎ ሰየማቸው ገብርኤልን አለቃ አድርጎ ሾመላቸው።
- በሁለተኛዋ ከተማ ያሉትን ***መናብርት*** ብሎ ሰየማቸው። ሩፋኤልን አለቃቸው አድርጎ ሾመላቸው።
- በሦስተኛው ከተማ ያሉትን ***ሥልጣናት*** ብሎ ሰየማቸው። ሱርያልን አለቃቸው አድርጎ ሾመላቸው።

ኤራርንም እንደ ራማ በሦስት ከተማ ከፋሏት በእያንዳንዱ ከተማ አሥር አሥር ነገድ አስፍሮባታል።

- በኤረር በመጀመሪያዋ ከተማ ያስፈራቸውን ***መኳንንት***፣ በሁለተኛዋ ከተማ ያሉትን ***ሊቃናት*** በሦስተኛዋ ከተማ ያሉትን ***መላእክት*** ብሎ ሰይሟቸዋል። ለመኳንንት ስዳካኤልን፣ ለሊቃናት ሰላታኤላን ለመላእክት አናንኤልን አለቃ አድርጎ ሾሞላቸዋል።

የነገደ መላእክትን ስም፣ አሥፋፈራቸውንና የአለቃቸውን ስም በሠንጠረዥ ይመልከቱ።

ሠንጠረዥ__________

| የሰማዩ ስም | የአሥሩ ነገድ ስም | የአለቃቸው ስም |
|---|---|---|
| ኢዩር | አጋዕዝት | ሳጥናኤል |
| | ኪሩቤል | ኪሩክ |
| | ሱራፌል | ሱራፌል |
| ራማ | ኃይላት | ሚካኤል |
| | አርባብ | ገብርኤል |
| | መናብርት | ሩፋኤል |
| | ሥልጣናት | ሱርያል |
| ኤራር | መኳንንት | ሰደካኤል |
| | ሊቃናት | ሰላታኤል |
| | መላእክት | አናንኤል |

*እሁድ ቀደማይ ሰዓተ መዓልት (እሁድ ከንጋቱ ፩ ሰዓት)*
እግዚአብሔር አምላክ ቅዱሳን መላእክትን ከፈጠራቸው በኂላ በባሕርዩ ረቂቅ ነውና አብሯቸው ሳለ ተሰወረባቸው፡፡ ይህም መላእክቱ ከእግዚአብሔር በአገኙት እውቀት ተመራምረው እርሱን ፈጣሪያቸውን እንዲያውቁ ነው፡፡ ከዚህ በኂላ መላእክት «ማን ፈጠረን» «ከወዴት መጣን» እያሉ መመራመር ጀመሩ፡፡ ሳጥናኤልም ከሁሉ በላይ ሆኖ ተፈጥሯልና ከወደታች መላእክት ይህን ሲነጋሩ ቢሰማ ከወደላይ ግን ድምጽን ቢያጣ «እኔ ፈጠርኳችሁ» ብሎ ሐሰትን ከራሱ አመንጭቶ ተናገረ፡፡ በዚህ ሰዓት በመላእክት ዘንድ ታላቅ ሽብር ሆነ፡፡ ከዲያብሎስ የሐሰት መዝገብ ከሆነ ልቦናው መንጭታ የወጣች ይህች የአመጽ ንግግር በአለቅነት የተሾመላቸው ፲ሩን ነገድ በሦስት ወገን ከፋፈላቻቸው፡፡ (ሄኖ ፲፩፥፫፤ ዮሐ ፰፥)

፩ኛ. አዎን ሳጥናኤል ፈጥሮናል ያሉ አንድ ወገን
፪ኛ. ፈጥሮን ይሆን ወይስ አልፈጠረን ይሆን እያሉ የተጠረጠሩ ሁለተኛ ወገን
፫ኛ. ከዚያም ከዚህም ሳይሆኑ እንዲሁ ፈዘው የቀሩ ሦስተኛ ወገን

የቀሩት ፺ቱ ነገድ ከነገደ ሚካኤል ተጨመረው እርሱ በቦታ በበላይነት ስለሆነ ፈጠረን ካለ እኛም የበታቾቻችንን ፈጠርናችሁ እንባልን? ይህስ አይሆንም አሉ፡፡ በዚህ ሰዓት መለአከ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል «ንቁም በበህላዌነ እስከ ነአምር ፈጣሪነ - ፈጣሪያችንን እስከምናቀው ድረስ በያለንበት ጸንተን እንቁም» ብሎ መላእክትን አረጋጋቸው፡፡
ሳጥናኤልንም ፈጠርኳችሁ ካልከን ፈጥረህ አሳየን አሉት፡፡ መፍጠር ተሳነው፡፡ በዚህ ጊዜ መላእክቱን ፈጽሞ እንዳያስታቸው ብሎ እሑድ በነግህ (ጠዋት ፩ ሰዓት) «ለይኩን ብርሃን - ብርሃን ይሁን» ብሎ ብርሃንን ፈጠረ፡፡ ብርሃኑን መዓልት ጨለማውን ሌሊት ብሎ ጠራው፡፡ (ዘፍ ፩፥፭)፡፡ መላእክትም ብርሃኑ ዕውቀት ሆኗቸው «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ እግዚአብሔር ምስጋናህ በሰማይና በምድር የመላ ነው» ብለው አመስግነውታል፡፡ ዲያብሎስና ያመኑበት መላእክት ግን ከክብራቸው ተዋርደዋል፣ ወደ ጥልቁም ተጥለዋል (ኢሳ ፲፬፥፲፪-፲፯)

*እሑድ ከጠዋቱ ፪ ሰዓት*
በዚህ ሰዓት መንፈስ ቅዱስ አንዱን ክንፉን ወደ ላይ አንዱን ክንፉን ወደታች አድርጎ ለመላእክት ታያቸው፡፡ «ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ ቅድስ ብለው ምሥጢረ ሥላሴን አምልተው አስድተው ተናገሩ፣ ሃይማኖታቸውንም አጸኑ፡፡»

*እሑድ ከቀኑ ፫ ሰዓት እስከ ቀኑ ፲፪ ሰዓት*
በነዚህ ሰዓታት ቅዱሳን መላእክትን በየነገዳቸው ከአጋዕዝት ጀምሮ እስከ መላእክት ያሉትን ቀባቸው፣ ማለትም እውቀት አእምሮን፣ የማያቋርጥ ምስጋናን ሰጣቸው፤ ሕማም ሞት ድካም እረፍት የሌለባቸው አደረጋቸው፡፡

## ፫ ፪ ፪ ዕለተ ሰኑይ (ሰኞ ዕለት)

> ሰኑይ ሰነየ ካለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ሁለት መሆንን፣ ሁለት ማድረግን ያመለክታል፡፡ ሰኑይ (ሰኞ) ሁለተኛ ዕለት ማለት ነው፡፡

በዚህ ዕለት እግዚአብሔር እሱን ዕለቱንና ጠፈርን ፈጥሮአል፡፡ ጠፈርን የፈጠረ በመጀመያው ሰዓተ ሌሊት (ከሌሊቱ በ ፩ ሰዓት) ነው፡፡ ጠፈር ከመፈጠሩ በፊት በዕለተ እሑድ የተፈጠረው ውሀ ከምድር እስከ ኤረር መልቶ አድሮ ነበር፡፡ ያንን ውኃ ከ፫ ወገን ከፍሎታል፡፡

፩ኛ. አንዱን እጅ በዚህ ዓለም አስፍሮታል
፪ኛ. ሁለተኛውን እጅ ከላይ አስፍሮታል፡፡ ይህም ውኃ ሐኖስ ይባላል፡፡
፫ኛ. ሦስተኛውን እጅ «ለይኩን ጠፈር ማእከለ ማይ ወማይ - በውኃና በውኃ መካከል ጠፈር ይሁን» ብሎ በመካከል አጽንቶታል፡፡

«በሁለተኛዩቱም ቀን በሐኖስና በውቅያኖስ መካከል ጠፈርን አድርጓልና። በዚያችም ቀን ውኃዎች ተከፋፍለው እኩሌቶቹ ወደ ላይ ወጥተዋልና፣ እኩሌቶቹ ከጠፈር በታች ወደአለው ወደ ምድር መካከል ወርደዋልና፣ በሁለተኛው ቀን ይህን ሥራ ብቻ ሠራ» እንዲል

(ኩፋ ፪፥፱)

## ፫ ፪ ፫ ዕለተ ሠሉስ (ማክሰኞ ዕለት)

ሠሉስ ሠለስ ሦስት አደረገ ከሰው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ ሦስተኛ ማለት ነው።

በዚህ ዕለትም እግዚአብሔር ራሱን ዕለቱንና ፫ ፍጥረታትን ፈጥሯል። (ዘፍ ፩፥፲፪) እነዚህም፦

፩ኛ. በመጥረቢያ የሚቆረጡ ዕፀዋትን /ዛፎችን…/
፪ኛ. በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕትን /ሣር መሰል ነገሮችን/
፫ኛ. በጣት የሚለቀሙ አትክልትን /ፍራፍሬዎችን . . ./

በዚህ ዕለት የዕለቱን ፍጥረታት ከመፍጠሩ በፊት አስቀድመው የተፈጠሩትን አደላድሏል . . . (ሽት )

## ፫ ፪ ፬ ዕለተ ረቡዕ (ረቡዕ ዕለት)

ረቡዕ ማለት አራተኛውን ዕለት የሚያመለክት ነው። በግዕዝ ራብዕ ማለት አራተኛ ማለት ነውና።

በዚህ ዕለት እግዚአብሔር ራሱን ዕለቱን እንዲሁም በመጀመሪያው ሰዓተ ሌሊት ቀኑንና ሌሊቱን ይለዩ ዘንድ ፫ ብርሃናትን በሰማይ ጠፈር ላይ ፈጥሯል። (ዘፍ ፩፥፲፬)። እነርሱም ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት ናቸው

የፀሐይ ተፈጥሮ ከእሳትና ከነፋስ ነው። ጨረቃና ከዋክብትን ግን ከነፋስና ከውኃ አርግቶ ፈጥሯቸዋል። ከዚህ በኋላ በዕለተ እሑድ «ለይኩን ብርሃን» በሎ ከፈጠረው ከደገኛው ብርሃን የስንዴን ቅንጣት ያህል አምጥቶ ያንን ከ፯ እጅ ከፋሎ ፮ቱን እጅ ለፀሐይ አደረገ። የቀረውን አንዱን እጅ እንደገና ከ፯ ከፋሎ ፮ቱን እጅ ለጨረቃ አደረገ። ቀረውን አንድ እጅ ለከዋክብት አደረገ። ከዋክብትንም በብርሃን ሲቀባ አላልቆ ነው።

«ኮከብ ከኮከብ በክብር ይበልጣልና» እንዲል።

(፩ ቆሮ ፲፭፥፵፩)

## ፫ ፪ ፭ ዕለተ ኀሙስ (ኀሙስ ዕለት)

ኀሙስ ኀመሰ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን አምስተኛ የሚል ትርጉም አለው።

በዚህም ዕለት ራሱን ዕለቱንና ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ፍጥረታት እንድታስገኝ ትዕዛዝ በመስጠት በደመ ነፋስ ሕይወት ሕያዋን የሆኑ ፫ ፋጥረታትን ፈጥሯል

እነዚህም፦ ፩ኛ. በልብ የሚሳቡ (ምሳሌ፦ ዓሣ አንበሪ)
፪ኛ. በእግር የሚሽከረከሩ (ምሳሌ፦ ዳክዬ)
፫ኛ. በክንፍ የሚበሩ (ምሳሌ፦ ዓሣ አውጭ) ናቸው።

## ፫ ፪ ፮ ዕለተ ዓርብ (ዓርብ ዕለት)

ዓርብ ዓርበ ካለው ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም መካተቻ ማለት ነው። ይህም ዕለቱ የፍጥረት መካተቻ፣ ማብቂያ/መፈጸሚያ መሆኑን ያመለክታል።

በዚህም ዕለት እግዚአብሔር ራሱን ዕለቱንና በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ከደረቅ ምድር በደመ ነፍስ ሕይወት ሕያዋን የሆኑ እንደ ኀሙስ ያሉ ፫ ፍጥረታትን ፈጥሯል። እነዚህም፦

፩ኛ. ሣር ነጭተው ውኃ ተጎንጭተው የሚኖሩ እንስሳት
፪ኛ. ሥጋ በጭቀው ደም ተጎንጭተው የሚኖሩ አራዊት እና
፫ኛ. ፍሬ ለቅመው ውኃ ጠጥተው የሚኖሩ አዕዋፍ ናቸው

በዕለተ ኀሙስና በዕለተ ዓርብ የተፈጠሩ ፍጥረታት «እንስሳት» በመባል አንድ ቢሆኑም በአኗኗራቸው ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ የኀሙስ ፍጥረታት በየብስ የአርብ ፍጥረታት በውኃ መኖር አይሆንላቸውምና፡፡
በዚሁ ዕለት በነግህ እግዚአብሔር «ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር›› ብሎ ፬ቱን ባሕርያተ ሥጋ ፭ኛ በሕርየ ነፋስን አዋሕዶ አዳምን ፈጥሮታል፡፡ (ዘፍ ፩÷፳፮) ከፈጠረውም በኋላ የሕይወት እስትንፋስን እፍ ብሎበታል፡፡ በዚህም ሰውን ከሌሎች በደመነፋስ ሕያዋን ሆነው ከሚኖሩ እንስሳት ለይቶ ክብርን ልጅነትን ሰጥቶ ለዘላለም ሕያው ፍጥረት አድርጎታል፡፡(ዘፋ ፪÷፯)

እግዚአብሔር እስከዝህ እስክ ፮ኛው ዕለት የፈጠራቸው ፍጥረታት ፳፪ ናቸው፡፡ እነዚህን ፈጥሮ ከፈጸመ በኋላ በ ፯ኛው ቀን አረፈ፡፡ (ዘፍ ፪÷፪፤ ኩፋ ፫÷፪ እና ፫)፡፡ አረፈ ማለትም ደክሞት አረፈ ማለት ሳይሆን መፍጠሩን ተወ ማለት ነው፡፡
ከዚህ በኋላ አዳም በተፈጠረ በ ፮ኛው ቀን በሁለተኛው ዓርብ ረዳት የምትሆን ሔዋንን ፈጠረለት፡፡ (ዘፍ ፪÷፲፰)

## ፫ ፫ ፳ው ዓለማት

እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ብዙውን አንድ እያለን ብንቆጥር ፳፪ ሥነ-ፍጥረት እንዳለ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከአራቱ ባህርያተ ሥጋ (እሳት፣ ውኃ፣ መሬት፣ ነፋስ) ፳ ዓለማትን ፈጥሯል፡፡ ፈጥሯል ስንልም አደላድሏል፣ አከናውኗል ማለት እንጂ ሌላ አዲስ ፍጥረትን አስገኝቷል ማለት አይደለም፡፡ እነዚህ ሃያው ዓለማት ከ ፳፪ቱ ሥነ-ፍጥረት ውስጥ ተካተው የሚቆጠሩ ናቸው እንጂ ከ ፳፪ቱ ሥነ-ፍጥረት ውጭ ሌላ ፍጥረታት አይደሉም፡፡
ሃያው ዓለማት የተፈጠሩት ከእሑድ እስከ ማክሰኞ ነው፡፡ ሃያው ዓለማት የሚባሉት ዝርዝራቸው በሠንጠረዥ ______________ተመልክቷል፡፡

| ተ.ቁ | የዓለማቱ ስም | ብዛት |
|---|---|---|
| ፩ | ዓለማተ እሳት | ፱ |
| ፪ | ዓለማተ ነፋስ | ፪ |
| ፫ | ዓለማተ ማይ | ፬ |
| ፬ | ዓለማተ መሬት | ፯ |
| ጠቅላላ ድምር | | ፳ |

### ፩ኛ. ዓለማተ እሳት

ዓለማተ እሳት የተፈጣሩት ከእሳት ግብር፣ ጠባይ (ብሩህነት፣ ውዑይነት፣ይቡስነት) ነው፡፡ የተፈጠሩበት ዕለትም ዕለተ እሑድ ነው፡፡ ዓለማተ እሳት በቁጥር ዘጠኝ ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- ሰባቱ ሰማያት (በገጽ ላይ ተመልክት)
- ምጽንዓተ ሰማይና
- ገሃነመ እሳት ናቸው

እግዚአብሔር ከእሳት ባህርይ ብሩህ ብሩሁን ወስዶ ሰባቱን ሰማያትንና ምጽንዓተ ሰማይን ፈጥሯል፡፡ ምጽንዓተ ሰማይ (የሰማይ መጽኛ ወይ መሠረት) እግዚአብሔር ሁሉም ሰማያት እንዲጸኑበት አድርጎ የፈጠረው የእሳት ጉዝጓዝ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የእሳቱን ዝቃጭ (ጨለማውንና ፍሙን) ወደ ታች አውርዶ ገሃነመ እሳትን ፈጥሮበታል፡፡

***፪ኛ. ዓለማተ ነፋስ***

ዓለማተ ነፋስ በነፋስ የተመሉ በነፋስ የረጉ የጸኑ ናቸው፡፡ የተፈጠሩትም በዕለተ ሰኑይ ነው፡፡
ዓለማተ ነፋስ የሚባሉት ሁለት ናቸው፡፡

- *ሀ* - **ባቢል፡-** ይህ የረጋ ነፋስ ከጠፈር በላይ የሚገኝ ሲሆን ሐኖስ ተብሎ የሚጠራውን ውኃ የሚሸከመው ነፋስ ነው፡፡
- **ለ** - ይህን ዓለም የሚሸከመው ነፋስ

***፫ኛ. ዓለማተ ማይ***

እነዚህ ዓለማት ከውኃ የተፈጠሩ ውኃ የመላባቸው ዓለማት ናቸው፡፡ የተፈጠሩትም በዕለተ ሰኑይና በዕለተ ሠሉስ ነው፡፡
ዓለማተ ማይ የሚባሉት ፬ ናቸው፡፡

፩ኛ. **ሐኖስ፡-** ይህ ብጽብጽ ውኃ የመላበት ከኤረር በታች የሚገኝ የውኃ ዓለም ነው ይህን የውኃ ዓለም ባቢል የሚባል ነፋስ ይሸከመዋል፡፡

፪ኛ. **ጠፈር፡-** ይህ ግግር ውኃ ነው፡፡ ጥንተ ባህርዩን በመጠኑ ስለለቀቀ እንደ አንድ ፍጥረት ተቆጥሯል

፫ኛ. **ውቅያኖስ፡-** ይህ መሬትን የሚከባት ውኃ ነው

፬ኛ. ከምድር በታች የሚገኝ ውኃ፡- ልበ አምላክ ዳዊት የምደር መሠረት ስለሆነው ስለዚህኛው የውኃ ዓለም እንዲህ ብሏል፡፡

«ምድርን በውኃ ላይ ያጸና»

(መዝ ፻፴፭፥፮)

ከአራቱ ዓለማተ ማይ ሐኖስና ጠፈር የተፈጠሩት በዕለተ ሰኑይ ሲሆን ውቅያኖስና የምድር መሠረት የሆነው የውኃ ዓለም የተፈጠሩት ደግሞ በዕለተ ሠሉስ ነው፡፡

***፬ኛ. ዓለማተ መሬት***

እነዚህ ዓለማት ከመሬት (ከአፈር) የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ዓለማተ መሬት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

***፩ኛ. ገነት፡-*** *ቀድሞ ከበደል በፊት አዳሞና ሔዋን የኖሩባት፤ ዛሬ በሃይማኖት ጸንተው ምግባር ሠርተው በሞተ ሥጋ ከዚህ ዓለም የተለዩ ቅዱሳን በአካለ ነፋስ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚቆዮባት የዕረፍት፣ የሕይወት የታድለና የደስታ ቦታ ናት፡፡*
በዚህች በገነት በፍሬ የተሞላች ፍሬዋን ለቅመው የማይጨርሱት፣ መዓዛ ጣዕሟ ልብን የሚመስጥ ***ዕፀ ሕይወት፤*** ከወተት ይልቅ እጅግ የሞትነጣ፣ ከማር ሰባት እጅ የምትጣፍጥ ***ማየ ሕይወት፤*** በአራቱ ማዕዘን ዞረው ገነትን የሚያጠጡ ***፬ቱ አፍላጋት*** (ወንዞች) ይገኙባታል፡፡

**፪ኛ. ብሔረ ሕያዋን፡-** አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉ ቅዱስን በአካለ ሥጋ እያሉ ከዚህች ዓለም እየተነጠቁ በመኄድ የሚኖሩባት ናት፡፡ ከነዚህ ቅዱሳን ሰዎች መካከል ጻድቁ ሄኖክንና፣ ነቢዮ ኤልያስን መጥቀስ ይቻላል፡፡ (ዘፋ ነገ)

**፫ኛ. ብሔረ ብዐዓን፡-** ይህች ዓለም ከገቢረ ኃጢአት ፍጹም የተለዩ የጽድቅ ሥራን ብቻ የሚሠሩ ብፁዓን ሰዎች በሕይወተ ሥጋ የሚኖሩባት ናት፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱ የብርሃን ምድር ናቸው፡፡ ከጠፈር ዝቅ ከምንኖርባት ምድር ከፍ ብለው የሚገኙ ሲሆን በዓይነ ሥጋ የማይታዩ (የተሠወሩ) ናቸው፡፡ ገነት በምሥቅ ብሔረ ሕያዋን በሰሜን ብሔረ ብፁአን በደቡብ አቅጣጫ ይገኛሉ፡፡

**፬ኛ. *የምንኖርበት መሬት፡-*** ከአዳም በደል በኂላ ለሰው ልጆች መኖሪያ ሆና የተሰጠች ናት፡፡

**፰ኛ. ሲኦል፡-** የጸና ጨለማ የሞላበት፣ የሚያቃጥል እሳት ያለበት በምዕራብ አቅጣጫ ያለ ቦታ ነው። ኃጢአትን ሲሠሩ የኖሩ ሰዎች ከሞተ ሥጋ በኋላ በአካለ ነፋስ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ እየተቀጡ የሚቆዩባት የቅጣት ቦታ ነች።

ከላይ የተዘረዘሩት ፰ቱ ዓለማተ መሬት በብርሃን መጠን፣ በጥራትና በንጽሕና ይበላለጣሉ። ከሲኦል እኛ ያለንበት ዓለም ብሩህ ጥሩና ንጹሕ ነው። እኛ ካለንበት ዓለም ብሔረ ብፁዓን፣ ከብሔረ ብፁዓን ብሔረ ሕያዋን ከብሔረ ሕይዋን ገነት ብሩህ ጥሩና ንጹሕ ነው።

### ፫ ፬ የምዕራፉ ማጠቃለያ

የፋጥረታት አስገኚ ልዑል እግዚአብሔር ከእሑድ እስከ ዓርብ ፍጥረታትን ፈጥሯል። በሰባተኛው ዕለትም መፍጠሩን ፈጽሞአል። እግዚአብሔር በእነዚህ ዕለታት የፈጠራቸው ፍጥረታት በሠንጠረዥ ____________ተጠቃለው ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ________________

| የዕለት | በዕለቱ የተፈጠሩ ፍጥረታት ብዛት | በዕለቱ የተፈጠሩ ፍጥረታት ዝርዝር |
|---|---|---|
| እሑድ | | |

ከነዚህ ከ ፳፪ ፍጥረታት መካከል ተካተው የሚቆጠሩ ሃያ ዓለማት አሉ።

እነዚህም ፱ ዓለማተ እሳት ፪ ዓለማተ ነፍስ ፬ ዓለማተ ማይና ፰ ዓለማተ መሬት ናቸው። ሠንጠረዥ _______________እነዚህን ዓለማት በቀላሉ ለማጥናት ይረዳል።

| የዓለማቱ ስም | ብዛት | የዓለማቱ ዝርዝር | ዓለማቱ የተፈጠሩበት ዕለት |
|---|---|---|---|
| ዓለማተ እሳት | 9 | - ድርሐ አርያም<br>- መንበረ መ. | |

# ምዕራፍ አራት

## አዕማደ ምሥጢር

በዚህ ምዕራፍ የሃይማኖት ምሰሶዎች ስለሆኑ ስለ አምስቱ አዕማደ ምስጢራት በዝርዝር እንመለከታለን።

### ፬-፩ የምሥጢር ፍቺ በቤተ ክርስቲያን

ምሥጢር፡- አመሥጠረ ሠወረ ካለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ዘይቤያዊ ፍቺው ለልብ ጓደኛ ብቻ የሚነገር በሁለት ሰዎች መካከል የሚቀር ማለት ነው። ይህን ዘይቤያዊ ፍቺ ግን ቤተ ክርስቲያን ምሥጢር አትለውም። ምክንያቱም እግዚአብሔር የማያውቀው በሰዎች መካከል ብቻ ተወስኖ የሚቀር ነገር የለምና ነው። ሐናንያና ሰጲራ ከሰው ሁሉ ሠውረው የሠሩትን እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስ እንደገለጸለት። (ሐዋ ፭፥፩-፲)

በቤተክርስቲያን አፈታት ምሥጢር ማለት፡-

> በምርምር ጥልቀት፣ በእውቀት ብዛት ሊደረስበት የማይችል፣ በሥጋ አእምሮ ሳይሆን በመንፈስ አእምሮ የሚረዱት ረቂቅና ጥልቅ ኀቡዕ (የተሰወረ) ነገር ማለት ነው።

### ፬-፪ ምሥጢር የተባሉበት ምክንያት

ምሥጢር ማለት ከእውቀት በላይ የሆነ በእምነት ብቻ የሚረዱት መሆኑን ተመልክተናል። አምስቱ አዕማደ ምሥጢራትም ምሥጢር መባላቸው ከመምህራን ተምረው በልቦና መርምረው የሚያምኗቸው በዓይን የማይታዩ፣ በእጅ የማይጨበጡ ነገሮች የሚነገሩባቸው በመሆናቸው ነው። ሰው እነዚህን ምሥጢራት የሚረዳው የማይታየውን በምታስረዳና ተስፋን በምታስረግጥ በእምነት ነው። አዋቂ ፍጥረት የሆነው የሰው ልጅ ሁሉን የመመርመርና የመረዳት ሥልጣን ከእምላኩ የተሰጠው ቢሆንም የፈጣሪውን ባሕርይውንና ግብሩን በሞላ ለመረዳት ውሉን ከሆነው አቅሙ በላይ ስለሚሆንበት በእምነት መቀበል ብቸኛ አማራጩ ነው።

### ፬-፫ አዕማድ የተባሉበት ምክንያት

<u>አዕማድ፡-</u> የሚለው ዐምድ የሚለው የግዕዝ ቃል ብዙ ቁጥር ነው። ዐምድ ማለት ትክል፣ ምሰሶ ማለት ነው። አዕማድ ማለት ደግሞ ምሰሶዎች ማለት ይሆናል።

ምስጢራቱ ምስሶዎች መባላቸው ምሰሶ ቤትን ደግፋ እንደሚያጸና እነዚህም ቤተ-ልቡናን ከኑፋቄ (በክህደት ከመውደቅ) የሚያጸኑ ስለሆነ ነው። ምሰሶ የሌለው ቤት ይፈርሳል፤ ይወድቃል። የቀና ሃይማኖት ያልተማረ፣ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር ያላወቀ ክርስቲያንም በክህደት በጥርጥር ይያዛል፣ ሃይማኖትን ባለመያዙ ምግባር ባለመሥራቱ በመንጸፈ ደይን ይወድቃልና ነው።

## ፬-፬ የአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ዝርዝር አከፋፈል

፭ቱ አዕማደ ምሥጢራት የሚባሉት፡-

፩. ምሥጢረ ሥላሴ
፪. ምሥጢረ ሥጋዌ
፫. ምሥጢረ ጥምቀት
፬. ምሥጢረ ቁርባን
፭. ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው

ምስጢረ ሥላሴና ሥጋዌ ነገረ መለኮት የሚነገርባቸው ናቸው፡፡ ይህም ማን የመለኮት ስሙን ግብሩን፣ ባህርዩን እንዲሁም ምስጢረ ትስብእትን (ሰው የመሆንን ምስጢር) የምንማርባቸው ናቸው፡፡

ምስጢረ ጥምቀትና ምስጢረ ቁርባን የቤተክርስቲያን ሀብታት ናቸው፡፡ ከ፯ቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መካከልም ናቸው፡፡

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ደግሞ ስለ ነገረ ሕይወት ማለትም ከሞት በኋላ ስላላ ሕይወት የምንማርባት ነው፡፡

በ ፭ቱ አዕማደ ምሥጢራት ሁሉን አካቶ ስለ እግዚአብሔር ባህርይና ጠባይዓት፣ ስለሰው ልጅ በኃጢአት መውደቅና ደግመኛ መዳን እንዲሁም ስለ ጽድቅና ኩነኔ መናገር ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ በእነዚህ በ ፭ቱ አዕማደ ምሥጢራት ሃይማኖትን መግለጥ የመረጠው፡፡

> «. . . ሌሎችን አስተምር ዘንድ በቋንቋ ከሚነገር ብዙ ቃል ይልቅ በቤተክርስቲያን በአእምሮዬ አምስት ቃላትን ልናገር እሻለሁ»

(፩ቆሮ ፲፬፥፱)

## ፬-፭ ምሥጢረ ሥላሴ

ሥላሴ፡- ሠለሰ ሦስት አደረገ ካለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን ሦስትነት፣ ሦስት መሆን የሚል ፍቺ አለው፡፡ የምሥጢርን ፍቺ በገጽ ተመልከት፡፡

ምስጢረ ሥላሴ ስንልም የአንድነት የሦስትነት ነገር የሚነገርበት ምስጢር ማለት ነው፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍትን አብነት በማድረግ ከቅዱሳን አበቶቻችን በተላለፈልን ትምህርት መሠረት እግዚአብሔርን በአንድነት በሦስትነት እናምነዋለን፤ እናመልከዋለን፡፡

### ፬-፭-፩ የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት

እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት፣ ሦስት ሲሆን አንድ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ይህ የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት በብሉያትና በሐዲሳት እንዴት እንደተገለጠ እንመለከታለን፡፡

***<u>በብሉይ ኪዳን</u>***

**ጥቅስ አንድ፡-**

> ‹‹እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር፡፡››

(ዘፍ ፩፥፳፮)

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ‹‹እግዚአብሔርም አለ›› ብሎ አንድነቱን፤ ‹‹ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር›› ብሎ ብዛቱን ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም ‹‹እንፍጠር›› የሚለው በፈጣሪነት ሥልጣን ትክክል (እኩል) የሆኑ አካላት የሚነጋገሩ መሆኑን ያሳያል፡፡

**ጥቅስ ሁለት፡-**

‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- እነሆ አዳም መልካምና ክፉን በማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፡፡”

(ዘፍ ፫፥፳፪)

እግዚአብሔር አለ ብሎ አንድነቱን ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ብሎ ከሁለት አካል በላይ እንደሆኑና ሥላሴ አንድ አካል አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡

በነገሥታት ልማድ ለመሊሉት “ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ” አለ እንጂ “ እንደ እኛ ሆነ “ ማለቱ ምላሽ ይሰጣቸዋል፡፡

እግዚአብሔርና ሚካኤል ናቸው ለሚሉትም አያስኬዳቸውም፡፡ “ እንደ እኔ ሆነ” እንደ አንተ ሆነ” መባል ነበረበትና፡፡

**ጥቅስ ሦስት፡-**

” እግዚአብሔርም አለ … ኑ እንውረድ አንዱም የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው፡፡”

(ዘፍ ፲፩፥፯)

“እግዚአብሔርም አለ“ በሚለው አንድነቱን፣ “ኑ እንውረድ” በሚለው ደግሞ አንዱ አካል ከአንድ በላይ ለሆኑ ሌሎች አካላት መናገሩን እንገነዘባለን፡፡

በተጨማሪም “ቋንቋቸውን እንደባልቀው” የሚለው የመፍረድ የመቅጣት ስልጣናቸው እኩል (አንድ) የሆኑ አካላት እንዳሉ ያሳያል፡፡

**ጥቅስ አራት፡-**

(ዘፍ ፲፰፥፩-፲)

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍለ ንባብ እግዚአብሔር ለአብርሃም በሦስት ሰዎች አምሳል መገለጹ ተመልክቷል፡፡ ይህም ቀደም ባሉት ጥቅሶች ግልጽ ሆኖ ያልተቀመጠውን የእግዚአብሔርን ሦስትነት ገሃድ ያደርገዋል፡፡

አብርሃምም ይናገረው የነበረው አንድነትንና ሦስትነትን የሚያሳይ ነው፡፡

- “ አቤቱ በፊትህ ሞገስን አግንቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ” ማለቱ ሦስቱ ሰዎች በጌትነት አንድ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ቀጠል አድርጎ…
- “ ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ” ማለቱ በሦስትነታቸው መናገሩ ነው
- “ ሦስት መስፈሪያ ዱቄት አዘጋጂ” ብሎ ሚስቱን ሣራን ሲያዛት ሦስትነትን “ለውሽውም እንጎቻም አድርጊ” ብሎ በአንድ ለውሳ እንጎቻ እንድትጋግር ማዘዙ ደግሞ የሦስቱን አንድነት ያጠይቃል፡፡

በተጨማሪም በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር ፱ ላይ፡- “እነርሱም፡- ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት አሉት” የሚለው ሦስትነታቸውን፤ “እርሱም የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ጊዜ እመለሳለሁ” የሚለው አንድነታቸውን ያመለክተናል፡፡

**ጥቅስ አምስት፡-**

“የእስራኤልን ልጆች ስትባርኳቸው እንዲህ በሏቸው፡፡ እግዚአብሔር ይበርክህ ይጠብቅህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም፡፡ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሳ ሰላሙንም ይስጥህ”

(ዘኁ ፯፥፳፫-፳፯)

ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር መባሉ ሦስትነትን፤ ቃሉ አንድ መሆኑ አንድነትን ያመለክታል፡፡ (ከ ፪ ቆሮ. ፲፫፥፲፬ ጋር በማቆራኘት)

“እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም” የሚለው ለእግዚአብሔር ወልድ የተነገረ ነው፡፡”

ይህም ማለት ቡሩክ እግዚአብሔር መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን አርቆልህ በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን ይስጥህ፣ በነፍስም በሥጋም ይጠብቅህ፣ ከክህደት ከጥርጥር ከሥጋዊ ጠላት፣ ከደብአ አጋንንት ከመርገም ከኩነኔ ከገሃነም ይጠብቅህ ማላት ነው። ይህም ያለ እግዚአብሔር ጸጋ አይገኝምና ቅዱስ ጳውሎስ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ" ብሎ ጠቅሶታል። "ጸጋስ ሥርየተ ኃጢአት ይእቲ" እንዲል ሰው ከኃጢአት እስራት የተፈታው፣ ከሲኦል የወጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ነውና።

"እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፣ ይራራልህም"

ሰው ወዳጁን በብሩህ ገጽ በፈገግታ ይቀበለዋል። ብሩህ ገጽ የፍቅር መግለጫ ነው። ርህራሄ ደግሞ ከፍቅር የሚመነጭ ነው። ምስጢሩም እግዚአብሔር እኛን በፍቅር አይን ተመልክቶ በርህራሄው ከመከራ እንደሚያድነን የሚያስረዳ ነበር። "የእግዚአብሔር ፍቅር" ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ለጠቀሰው ነው። (በተጨማሪ ዮሐ. ፫፣፲፮፤ ፩ዮሐ ፫፣፩፱)

"እግዚአብሔር ፊቱን ወዳንተ ያንሳ ሰላሙንም ይስጥህ"

ይህም በምህረት ዓይን ይመልከትህ፤ በውስጥ በአፍአ፣ በነፍስ በሥጋ ሰላምን ይስጥህ ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ "የመንፈስ ቅዱስ ሕብረት" ያለው ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሰላም ሲል። ሰላም የሚገኘው ሕብረት ባለበት ነውና። ሰላምና ሕብረት፤ ጸብና መለያየት አይነጣጠሉምና።

**ጥቅስ ስድስት:-**

"የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደደረገችኝ፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች"

(መዝ ፻፲፯፥፲፮-፲፯)

የእግዚአብሔር ቀኝ የሚለው ሦስት ጊዜ መነገሩ የሦስትነት፤ ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ነው።

**ጥቅስ ሰባት:-**

"እግዚአብሔር ታላቅ ነው። ኃይሉም ታላቅ ነው። ለጥበቡም ቁጥር የለውም"

(መዝ ፻፵፮፣፭)

- ይህም ማለት:- እግዚአብሔር አብ ገናና ነው፤ ኃይሉ እግዚአብሔር ወልድም ገናና ነው፤ ኃይሉ አለው ኃይሉ ስለተገለጸበት፣ በኃይል አንድ ስለሆኑ። ጥበቡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ሀብቱ ፍጹም ነው። መንፈስ ቅዱስ ሀብቱ ብዙ ነውና ስፍር ቁጥር የሌለው ጥበብ ብሎ መንፈስ ቅዱስን አነሳ። (ኢዮ ፱፣፬)

**ጥቅስ ሰባት:-**

"አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድርም ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር።"

(ኢሳ. ፮፣፫)

ሦስት ጊዜ ቅዱስ መባሉ የሦስትነት ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ ነው። በሌላም መልኩ ሦስት ጊዜ ቅዱስ መባሉ የሦስትነት ቃሉ አለመለወጡ ሦስቱ አካላት በምስጋና ትክክል መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

ድግግሞሽ ነው እንዳይባል በዕብራውያን የአነጋገር ዘይቤ ደጊመ ቃል ሁለት ጊዜ ነው እንጂ ሦስቴ አይደለም። (ዘፍ ፳፪፥፲፩፤ ዘጸ ፫፥፬፤ ፩ሳሙ ፫፥፲)

**ጥቅስ ስምንት:-**

"የጌታንም ድምጽ:- ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁት"

(ኢሳ. ፮፣፰)

ማንን እልካለሁ? የሚለው አንድነቱን፣ ማንስ ይሄድልናል? የሚለው ደግሞ ሦስትነቱን ያሳያል።

በተጨማሪም የሚከተሉት የብሉይ ኪዳን ምንባባት የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚያሳዩ ናቸው።

- ኢሳ ፵፰፥፲፪-፲፮ - ጦቢ ፰፥፮ - ሲራ ፫፥፳፪
- መዝ ፴፪፥፫-፯ - ዘፍ ፪፥፲፰

*በሐዲስ ኪዳን*

የአንድነቱና የሦስትነቱ ነገር በብሉይ ኪዳን በምሥጢር የታወቀ ቢሆንም በሐዲስ ኪዳን ግን በግልጽ ተቀምጧል።

**ጥቅስ አንድ፡-**

"ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ። እነሆም ሰማያት ተከፈቱ። የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ። እነሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።"

(ማቴ ፫፥፲፮-፲፯)

ሰማይ ተከፈተ መባሉ ደጅ በተከፈተ ጊዜ የውስጡ እንዲታይ እስከ አሁን ያልተገለጠ ምስጢር ታየ፣ ተገለጠ ለማለት ነው

ጌታ ሲጠመቅ ሦስት አካላት በአንድ ሰዓት /ጊዜ/ ተገኝተዋል። አንዱ አካል ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ሲወጣ፤ መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካሉ በአምሳለ ርግብ ሲወርድ፤ አካላዊ አብ በተለየ አካሉ በደመና ሆኖ ሲመለከት፣ የወደደው ለተዋህዶተ ሥጋ ወደ አለም የላከው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሲናገር ሦስትነት ተረድቷል።

**ጥቅስ ሁለት፡-**

"እንግዲህ ሂዱና አህዛብን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው።

(ማቴ ፳፰፥፲፱)

ይህ ጥቅስ የሥላሴን የስም ሦስትነት (ሥላሴ በስም ሦስት መሆናቸውን) ይገልጻል።

**ጥቅስ ሦስት፡-**

"መንፈስ ቅዱስ በአንደቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፣ ስለዚህ ደግሞ ካንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።"

(ሉቃ ፩፥፴፭)

**ጥቅስ አራት፡-**

" እነሆም በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም የመንፈስ ቅዱስም ስም በግንባራቸው ላይ የተጻፈላቸው...."

(ራዕ. ፲፬፥፩-፪)

በግ ያለው ለሰው ልጆች ቤዛ የሐዲስ ኪዳን መስዋዕት ሆኖ የቀረበውን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ስለጌታችን ሲመሠክር፡-

"እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" እንዳለ።

(ዮሐ ፩፥፴፯)

**ጥቅስ አምስት፡-**

"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ።"

(ራዕ. ፬፥፰)

ለትንቢተ ኢሳይያስ ፮፣፫ የተሰጠውን ማብራሪያ በገጽ ተመልከት

## አንድነት በምን?

ሥላሴ በህልውና፣ እግዚአብሔር በመባል፣ በአምላክነት፣ በአገዛዝ፣ በሥልጣን፣ በመለኮት፣ በባህርይ፣ በልብ፣ በቃል በእስትንፋስ አንድ ናቸው። እነዚህንም በመሳሰሉት ሁሉ አንድ ናቸው።

"እኔና አብ አንድ ነን።" እንዳለ።

(ዮሐ. ፲፥፴)

### (ሀ) ሥላሴ በህልውና (በአኗኗር) አንድ ናቸው።

ህልውና ማለት አንዱ በአንዱ መኖር ማለት ነው። ይኸውም በኩነታት (በሁኔታዎች) የሚገናዘብ ረቂቅ ምስጢር ነው።

‹‹እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳ አታምኑምን?... እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ››

(ዮሐ. ፲፬፥፲ እና ፲፩)

ሥላሴ በህልውና አንድ ስለሆኑ (አንዱ በአንዱ ስላለ) አብ ተጠራ ማለት አብን በተለየ አካሉ መጠቆም ቢሆንም ወልድና መንፈስ ቅዱስም በአብ ህልውና አሉ። ለወልድም ለመንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ነው። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሥራው የሦስቱም ሆኖ ሳለ ለአንዱ አካል ሰጥቶ የሚናገረው።

- *ለአብ ሰጥቶ ሲናገር*

" እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል"

(ዮሐ. ፲፬፥፰)

ሥራውን ለአብ ሰጥቶ መናገሩ ቅድመ ዓለም በአብ ልብነት የታሰበውን በእኔ ቃልነት እናገራለሁ ለማለት ነው። ሥራው የሦስቱም ሆኖ ሳለ ለአብ ሰጥቶ መናገሩ በአብ ህለውና ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስላሉ በአብ የሁሉንም መናገር ነው እንጂ አብ ብቻውን ይሠራል ማለት አይደለም። አብ ያለ ወልድ ምንም ሥራ እንደማይሠራ ".... ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም" ተብሎ ለእግዚአብሔር ወልድ ተነግሯል (ዮሐ.፩፥፫)

- *ለወልድ ሰጥቶ ሲናገር*

"... እኔ በፈቃዴ እኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ስልጣን አለኝ ደግሞም ላነሳት ስልጣን አለኝ።"

(ዮሐ. ፲፥፲፰)

ስልጣን የሁሉም ሲሆን ለወልድ ሰጥቶ ይናገራል። በወልድ ህልውና አብና መንፈስ ቅዱስ ስላሉ የእነርሱንም የስልጣን ባለቤትነት መናገር ነው። ለዚህ ነው ሥልጣኑ የአብም ሥልጣን ስለሆነ እንዲህ የተባለው፡-

"...ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሳው"

(ሐዋ. ፪፥፴፪)

- *ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ ሲናገር*

" ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል። እርሱ ያከብረኛል ለእኔ ካለኝ ወሰደ ይነግራችኋልና። ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ስለዚህ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል።"

(ዮሐ ፲፮፥1፫-1፭)

መሪነት የሁሉም ሆኖ ሳለ ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ ይናገራል። በመንፈስ ቅዱስ ህልውና አብና ወልድ ስላሉ የእነርሱንም መሪነት መናገር ነው። በህልውናም አንድ ስለሆኑ "ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው" ይላል።

የህውልና አንድነት በዮርዳኖስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅም ተገልጧል። ሦስቱ አካላት በዮርዳኖስ በአንድ ጊዜ ሲገኙ ህልውናቸው ደግሞ አብ በወልድ ቃልነት በመንፈስ ቅዱስ አስትንፋስነት ‹‹የምወደው የምወልደው ልጄ እርሱ ነው እርሱን ስሙ ብሎ›› በመናገሩ ታውቋል።

የሥላሴን የህልውና አንድነት በሰው ልጅ ባሕርይ ምሳሌነትም ይረዱታል፡፡ ለእኛ ለሰው ልጆች ሦስት ነገር አለን፡፡ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ፡፡ በልቦናችን አብ፣ በቃላችን ወልድ፣ በእስትንፋሳችን መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡
በልቦናችን እንደምናስብ ሥላሴም በአብ ልቦናነት ያስባሉ፤ በቃላችን ቃል እንድንናገር በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፤ በእስትንፋሳችን እንደምንተነፍስ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ይተነፍሳሉ፡፡

ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ የሥላሴ የባህርይ ከዊን /ሁኔታ/ ስማቸው ነው፡፡ ይህም የኩነታት (የሁኔታዎች) ሦስትነት በህልውና የሚገናዘቡበት /አንዱ በአንዱ ውስጥ የሚገኙበት/ ስም ነው፡፡

- አብ ለራሱ ለባዊ (አዋቂ) ሆኖ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ልብ እውቀት ነው፡፡ በእርሱ ልብነት ወልድ መንፈስ ቅዱስ ህልዋን ናቸው፤ ያስቡበታል፡፡
- ወልድ ለራሱ ነባቢ (ቃል) ሆኖ ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ ቃል ነው፡፡ በእርሱ ቃልነት አብ መንፈስ ቅዱስ ህልዋን ናቸው፤ ይናገሩበታል፡፡
- መንፈስ ቅዱስ ለራሱ ህያው ሆኖ ለአብ ለወልድ ህይወት ነው፡፡ በእርሱ እስትንፋስነት አብ ወልድ ህልዋን ናቸው፤ ሕያዋን ሆነው ይኖሩበታል፡፡

ከዚህ ወጥቶ ግን ለሦስቱ አካላት ለየራሳቸው ልብ፣ቃል፣ እስትንፋስ አላቸው ማለት ክህደት ነው፡፡

**(ለ) ሥላሴ በእግዚአብሔርነት(እግዚአብሔር በመባል) አንድ ናቸው፡፡**

አብ እግዚአብሔር ይባላል፤ ወልድ እግዚአብሔር ይባላል፤ መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ይባላል፡፡ ነገር ግን አንድ እግዚአብሔር ቢባል እንጂ ሦስት እግዚአብሔር አይባልም፡፡

"… አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፡፡" እንዲል፡፡

(ዘዳ. ፮፥፬)

የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ሦስቱም አካላት እግዚአብሔር እንደሚባሉ (እግዚአብሔር በመባል አንድ እንደሆኑ) ያሳያሉ፡፡

- አብ እግዚአብሔር ተብሎ እንደሚጠራ፡-
  "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ **የእግዚአብሔርም** ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ህብረት…"
  (፪ቆሮ. ፲፫፥፲፬)
- ወልድ እግዚአብሔር እንደሚባል፡-
  "በገዛ ደሙ የዋጀትን **የእግዚአብሔርን** ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ…"
  (ሐዋ. ፳፥፳፲)
  አማናዊት ቤተክርስቲያንን በደሙ ፈሳሽነት የዋጃትና የመሠረታት እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡
- መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሚባል፡-(ሐዋ. ፭፥፫-፬)
  "ጴጥሮስም፡- ሐናንያ ሆይ **መንፈስ ቅዱስን** ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ?… **እግዚአብሔርን** እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው"
  ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናንያን ያታለለው/የዋሸው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንደሆነ ነግሮታል፡፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሚባል ያሳያል፡፡
  . (ዕብ. ፫፥፯) (ዘጸ. 12፣2) ሁለቱን በማገናዘብ ተመልከት

ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን መጻፍ ሲጀምር ሦስቱንም አካላት እግዚአብሔር ብሎ በመጥራትና የህልውናቸውን ቅድምና በመመስከር ነው፡፡

"በመጀመሪያ ቃል ነበር፡፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፡፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበር፡፡ ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፡፡"

(ዮሐ. ፩፥፩-፪)

ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር ማለቱ ሦስቱም አካላት እግዚአብሔር መባል የሚገባቸው በመሆናቸው ነው፡፡

**(ሐ) ሥላሴ አምላክ በመባል አንድ ናቸው፡፡**

አብ አምላክ ይባላል፤ ወልድ አምላክ ይባላል፤ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ይባላል። ነገር ግን አንድ አምላክ ቢባል እንጂ ሦስት አምላክ አይባልም።

"ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።"

(ኤፌ. ፬፥፯)

በተጨማሪም የሚከተሉት ምንባባት አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ ያሳያሉ። (፩ጢሞ ፩፥፲፯፤ ኢሳ. ፵፥፳፰)

**(መ) ሥላሴ በፈጣሪነት አንድ ናቸው።**

(ዘፍ. ፩፣፩) "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ"። "ፈጠሩ" አላለምና

- (መዝ. ፪፩፣፳፩) "አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው።

ሥላሴ በመፍጠር አንድ በመሆናቸው ‹‹እግዚአብሔር ፈጠረ›› ብሎ አንድ ፈጣሪ መኖሩን እየተናረ በህልውና አንድ ናቸውና ፈጣሪነትን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ ይናገራል። (ስለ ህልውና አንድነት በገጽ የተሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት)

- (ኢዮ. ፴፫፣፬) "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ" ሲል መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ መሆኑን
- (ዮሐ. ፩፥፫) " ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም" ሲል ወልድ ፈጣሪ መሆኑን
- (መዝ. ፪፣፯) "የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ፤ ሠራዊቱም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ።" ሲል ሦስቱም አካላት ፈጣሪ መባል የሚገባቸው መሆኑን ያሳያል።

## ሦስትነት በምን?

ሥላሴ በስም በአካል፣ በግብር ሦስት ናቸው።

አካልና ስም ቋንቋዊ ፍቻቸውን ስንመለከት፦

- **አካል**፦ ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር በሥጋ በአጥንት በጅማት በቁርበት የተያያዘ **ገጽን መልክዕን አቋምን** ያሳያል።
  - **ገጽ**፦ ልብስ የማይሸፍነው ከአንገት በላይ ያለውን መገለጫ ወይም በአጭሩ ፊትን ያመለክታል። መለያ መታወቂያ ማለት ነው።
  - **መልክዕ**፦ ኀብርን፣ ቅርጽን፣ ደምግባትን ያመለክታል። ይኸውም ቀይ መልክ፣ ጥቁር መልክ፣ መልከ መልካም፣ መልከ ክፉ ሲል ይታወቃል።
- **ስም**፦ ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ያለው አንድ አካል ከሌላ አካል ተለይቶ ማን እንደሆነ ታውቆ የሚጠራበት ነው።

  ስም ስንልም ሦስት ዓይነት ነው።

  ሀ- **የተጸውዖ ስም**፦ አንዱ ከሌላው ተለይቶ የሚጠራበት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ ለሆኑ ተመሳሳይ ባህርይ ላላቸው የሚሰጥ ስም ነው። በሌላ ሁለተኛ ወገን የሚሰጥ ስለሆነ በአብዛኛው ዋናው አገልግሎቱ ከብዙዎቹ ተመሳሳይ አካላት አንዱን ለይቶ ለመጥራት ነው።

  ለ - **የግብር ስም፦** በአካል ተቀድሞ የአካልን እንቅስቃሴ ጠባይና ሥራ የመሳሰሉትን የሚያመለክት ነው።

  ለምሳሌ፦ ገበሬ፣ ሰዓሊ …

  ሐ- **የአካል ስም፦** ይህ ስም የሚነሳው ከባህርይ በመሆኑ በአካል የሚቀዳም ሳይሆን ከአካለ ጋር እኩል ህላዌ ያለው ስም ነው።

  **ለምሳሌ**፦ ሰው፣ ፈረስ፣ አንበሳ እንደማለት ሲሆን ይህን ስም ያገኙት አካል ሲገኝ ጀምሮ ነው እንጂ ኖረው ኖረው አይደለም፡

### ሀ) የሥላሴ የአካል ሦስትነት

ሥላሴ በአካል ሦስት ናቸው። ይህም ማለት ለአብ ፍጹም አካል ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ አለው። ለወልድም ፍጹም አካል ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ አለው። ለመንፈስ ቅዱም ፍጹም አካል ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ አለው።
ሰው በአርአያ ሥላሴ ተፈጥሯልና የሥላሴ አካል መገለጫ ነው። ለዚህ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር በሰው አካል አምሳል እጅ እግር፣ አይን፣ ጆሮ እንዳሉት የተጻፈው።

"የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ነውና።"

(መዝ. ፴፫፣፲፭)

"… ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት"

(ኢሳ. ፷፮፥፩)

ይህ ማለት ግን በእግዚአብሔር አካልና በሰው አካል መካከል ልዩነት የለም ማለታችን አይደለም። ትልቅ ልዩነት አለ። ይህንንም ልዮነት በሠንጠዥ ተመልከት

| የሰው አካል | የሥላሴ አካል |
|---|---|
| ግዙፍ ነው | በዓይን አይታይም፤ በህሊናም አይታሰብም፤ ረቂቅ ነው |
| ውሱን ነው | በሰማይና በምድር በአየርና በዕመቅ የመላ ነው፤ በሁሉም ቦታ አለ። |
| ጠባብ ነው | ስፉህ /ሰፊ/ ነው። ለስፋቱም ልክና መጠን የለውም፤ ላይና ታች ቀኝና ግራ የለውም |
| ፈራሽ በስባሽ ነው (ዘፍ. ፫፥1፱፤ መዝ.፻፪፥፲፬) | ይህ የሌለበት ሕያወ ባህርይ ነው (ራዕ ፩፥፲፰) |
| ደካማ ነው | ሁሉን ቻይ ድካም የሌበት ነው (ኢሳ ፵፥፳፲) |
| አስገኚ አለው | አስገኝ የሌለው ነው |

በአጭሩ ሰው ሥጋ ለባሽ ስለሆነ ግዙፍና ተዳሳሽ አካል ሲኖው እግዚአብሔር ግን መንፈስ በመሆኑ ረቂቅና የማይዳሰስ አካል አለው።

የእግዚአብሔርን የአካል ሦስትነት ስናስብ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ለእየራሳቸው ፍጹም አካል ስላላቸው ሦስቱም በተለየ አካላቸው እኔ ማለት የሚቻለቸውና እርሱ የሚባልላቸው ናቸው።

"እኔ ፊተኛው ነኝ፤ እኔ ኋለኛው ነኝ…ከሆነበትም ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ። አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል።"

(ኢሳ. ፵፲፣ 1፪-1፮)

"እኔ ፊተኛው ነኝ" ያለ በተለየ አካሉ ሰው ሆኖ የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የላከውን አብን እግዚአብሔር ብሎ መንፈስ ቅዱስን ደግሞ መንፈሱ ብሎ አነሳ። በአካል ፍጹን ናቸውና "ልከውኛል" አለ።
በሌላም የወንጌል ክፍል እንዲህ የሚል ተጽፏል።

"እኔም አብን እለምናለሁ። ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል። እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይችለው የእውነት መንፈስ ነው"

(ዮሐ. 10፣ 18-12)

"ሌላ አጽናኝ" መባሉም፦ አብ አጽናኝ ነው ልጁን ወደ ዓለም የላከ ነውና፤ ወልድም አጽናኝ ነው ዓለምን ለማዳን የመጣ ነውና፤ ከሁለቱም ሌላ ፍጹም አካል ያለው ለማለት ነው።
በተጨማሪም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል፦

"ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህንን ነግሬአችኂለሁ፤ አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኂል።"

(ዮሐ› 10፤፳፮)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ ሦስቱም አካላት በአንድ ቦታ በአንድ ሰዓት መገኘታቸውም ሥላሴ በአካል ፍጹማን ለመሆናቸው (ለእየራሳቸው አካል ያላቸው ለመሆኑ) ተጨማሪ ማስረጃ ነው። (ማቴ. ፫÷፲፮ እና ፲፯)

## ለ) የሥላሴ የስም ሦስትነት

ሥላሴ በስም ሦስት ናቸው። የስም ሦስትነታቸውም አብ፣ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነው።

- አብ ማለት አባት፣ አሥራዒ ማለት ነው። ወልድን የወለደ፣ መንፈስ ቅዱስን ያሰረጸ ነውና
- ወልድ ማለት ልጅ ማለት ነው፤ የአብ የባህርይ ልጅ ነውና
- መንፈስ ቅዱስ ማለት ሠራፂ (የተገኘ፣ የወጣ) ማለት ነው። ከአብ አብን መስሎ ወልድን አህሎ የሠረፀ ነውና፡

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚለው የሥላሴ የአካል ስማቸው ነው። ምንም እንኳ ሥላሴ በዚህ ጊዜ ተገኙ ባይባልም፤ ጥንት መሠረት ሳይኖረው ቅድመ ዓለም ሲርኖ የኖረ ነው እንጂ እንደተጸውዖ ስም ኖሮ ኖሮ የወጣ አይደለም። የሥላሴ አካል ጥንት እንደሌለው ሁሉ ለስሙም ጥንት የለውም።

አብ ተለውጦ ወልድን መንፈስ ቅዱስን እንደማይሆን የአብ ስሙ ተለውጦ ወልድ መንፈስቅዱስ አይባልም። ለአብ የአባትነት ስም የአባትነት ክብር አለውና። ወልድም ወልድ ቢባል እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ አይባልም፤ የባህርይ ክብሩ ከአብ ሳያንስ የልጅነት ክብር የልጅነት ስም አለውና። መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ቢባል እንጂ አብ ወልድ ተብሎ አይጠራም። የባህርይ ክብሩ ከአብ ከወልድ ሳያንስ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ይጠራል እንጂ።
የሥላሴ የስም ሦስትነት በብሉያትም በሐዲሳትም ተመስክሯል።

**በብሉይ ኪዳን**

"እግዚአብሔር አለኝ፦ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ"

(መዝ. ፪÷፯)

ቅድመ ዓለም አካል ዘእምአካል፣ ባህርይ ዘእምባህርይ የወለድኩህ ልጄ ነህ አለኝ። ዛሬም በተዋህዶ የወለድኩህ ልጄ ነህ አለኝ ብሎ አብና ወልድን ያነሳል። ተናጋሪው ወልድ ነው፤ እግዚአብሔር ብሎ አብን አንስቷል።

(መዝ. ፴፪÷፮)

በምስጢረ ሥላሴ ትምህርት አብ ልብ፤ ወልድ ቃል መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ናቸውና እንዲህ አለ።

"ይህን ታውቅ እንደሆንህ፤ ስሙ ማን የልጁስ ስም ማን ነው?"

(ምሳ. ፴÷፬)

ይህ ቃል አብ የአባትነት፤ ወልድ የልጅነት ስም እንዳላቸው ያሳያል።

**በሐዲስ ኪዳን**

" ሒዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኂቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው"

(ማቴ ፳፰÷፲፱)

" እርሱ የእውነት **መንፈስ** በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ያመራችኂል... እርሱ ያስከብረኛል። ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኂልና **ለአብ** ያለው ሁሉ የእኔ ነው።"

(ዮሐ. ፲፮÷፲፫-፲፭)

ሥላሴ በክብር በስልጣን አንድ ስለሆኑ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተብለው ሲጠሩ የስልጣን ቅደም ተከተል የሚያሳይ አይደለም።

> "የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ሕብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን"

(፪ቆሮ. 1፫፣10)

ይህ የመጽሐፍ ቃል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወልድን አስቀድሞ፤ አብና መንፈስ ቅዱስን አስከትሎ ሲጠራ ያሳያል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም አብን አስቀድሞ መንፈስ ቅዱስንና ከዚያም ወልድን አስከትሎ ሲጠራ የሚከተለው ምንባብ ያሳያል።

> "... እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ፣ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ..."

(፩ጴጥ. ፩፣፪)

## ሐ) የሥላሴ የግብር ሦስትነት

ግብር ማለት ሥራ ማለት ነው፣ ሥላሴ በግብር ሦስት ናቸው።

- የአብ ግብሩ ወልድን መውለድ መንፈስ ቅዱስን ማሥረጽ ነው
- የወልድ ግብሩ ከአብ መወለድ ነው።
- የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ ከአብ መስረጽ ነው።

አብ ቢወለድ ቢያሠርፅ እንጂ እንደ ወልድ አይወለድም፤ እንደ መንፈስ ቅዱስ አይሠርፅም። ወልድም ቢወለድ እንጅ እንደ አብ አይወልድም አያሠርፅም፤ እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሠርፅም። መንፈስ ቅዱስም ቢሠርፅ እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርፅም እንደ ወልድም አይወለድም።

ወላዲ አሥራዊ፤ ተወላዲ፤ሠራዊ የሚለው የሥራሴ የአካል ግብር ስማቸው ነው። ይህም በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት የተረጋገጠ ነው።

> " በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው **ልጄ** ይህ ነው"

(ማቴ. ፫፥፲፯)

ይህ ቃል አብ ወልድን እንደወለደ ያሳያል።

> "እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም **ከአብ የሚወጣ የእውነት** መንፈስ..."

(ዮሐ. ፲፭፥፳፮)

ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደሠርፀ ያሳያል።

አብ ወልድን ቢወልድ መንፈስ ቅዱስን ቢያሠርፅ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ በፊት ነበር አያሰኝም። በእኛ ልማድ (ግዕዝ) አባት ሲበልጥ ሲቀድም፤ ልጅ ሲተካ ሲከተል ነው። በሥላሴ ግን አብን አባት ወልድን ልጅ መንፈስ ቅዱን ሠራዊ ስላለን መቅደም መቀዳደም፤ መተከተል መከታተል፤ መብለጥ መበላለጥ የለባቸውም። የውስጥ የባህርይ ግብር ነውና።

## ፬-፭-፪ ስለ ምስጢረ ሥላሴ የሚያስረዱ ተፈሯዊ ምሳሌዎች

### ሀ. የሰው ምሳሌነት

የሰው ነፍስ ሦስትነት አላት። ልብነት ፣ቃልነት፣ሕይወትነት። በልብነቷ የአብ፣ በቃልነቷ የወልድ፣ በሕይወትነቷ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነች።

- ነፍስ እነዚህ ሦስት ነገሮች ስላሏት ሦስት ነፍስ እንደማትባል ሥላሴም በአካል ሦስት ቢሆኑም አንድ እግዚአብሔር አንድ አምላክ ቢባሉ እንጂ ሦስት እግዚአብሔር ሦስት አምላክ አይባሉም።
- የነፍስ ልብነቷ ቃልነቷን ሕይወትነቷን ከራሷ ታስገኛለች። ቃልና ሕይወት ከአንዲት ልብ ስለተገኙ በከዊን (በመሆን) ልዩ እንደ ሆኑ ሁሉ በመነገርም ይለያሉ። ቃል ተወለደ

እስትንፋስ ሡረፀ (ወጣ) ይባላል፡፡ እንደዚሁ አብ ወልድን በቃል አምሳል ወለደው፤ መንፈስ ቅዱስን በእስትንፋስ አምሳል አሠረፀው፡፡

- ነፍስ ስትገኝ በሦስትነቷ በአንድ ጊዜ ተገኘች እንጂ ልብነቷ ቀደሞ ቃልነቷና እስትፋስነቷ በኋላ የተገኙ አዩደሉም፡፡ እንደዚሁ አብ ወልድን ሲወልደው መንፈስ ቅዱስን ሲያሠርጸው አይቀድማቸውም

ሰው በነፍሱ በዚህ እኳኋን እግዚአብሔርን ስለሚመስለው "ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር" ብሎ ተናገረ (ዘፍ. ፩፣፳፮)

### ለ. የፀሐይ ምሳሌነት

ለፀሐይም ሦስትነት አላት፡፡ ክበብ፣ብርሃንና ሙቀት፡፡ በክበቧ አብ፤ በብርሃኗ ወልድ በሙቀቷ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡

- የፀሐይ ብርሃን የፀሐይ ክበብ፤ የፀሐይ ሙቀት ብለን ሦስት ጊዜ ፀሐይ ፀሐይ ማለታችን ለፀሐይ ሦስትነት እንዳለት ያሳያል እንጂ ሦስት ፀሐይ አለ እንደማያሰኝ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤ አብ አምላክ፣ ወልድ አምላክ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ማለታችንም ሦስት እግዚአብሔር ሦስት አምላክ አያሰኝም፡፡ (መዝ. ፲፰፥፬)
- የፀሐይ ክበቧ ብርሃኗንና ሙቀቷን ያስገኛል፤ ሆኖም ግን ብርሃንንና ሙቀትን ቀድሞ የሚገኝበት ጊዜ የለም፡፡ እንደዚሁም ሁሉ አብ ወልድን ቢወልድ መንፈስ ቅዱስን ቢያሰርፅ ወልድና መንፈስ ቅዱስን ቀድሞ የኖረበት ጊዜ የለም፡፡ በሥላሴ ዘንድ መቅደም መቀዳደም የለም፡፡
- ክበብ ብርሃኑን ፈንጥቆ ጨለማን በማራቁ፣ ዋዕዮን (ሙቀቱን) ልኮ በማሞቁ ህልውናውን (መኖሩን) እንዲያሳውቅ የአብም ህልውናው በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስለተገለጸ አብን ላኪ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስን ተላኪ አልን እንጂ በሥላሴ መብለጥ መበላለጥ ኖሮባቸው አይደለም

### ሐ. የእሳት ምሳሌነት

እሳትም አንድ ሲሆን ሦስትነት አለው፤ አካሉ፣ ብርሃኑና ሙቀቱ፡፡ በአካሉ አብ፣በብርሃኑ ወልድ፣ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡ "እሳት አምጣ" ሲባል ብርሃኑን "እሳት አብራ" ሲባል ብርሃኑን "እሳት እንሙቅ" ሲባል ሙቀቱን መናገር ነው፡፡ በዚህም ለእሳት ሦስትነት እነዳለው እንረዳለን፡፡

- እሳት አንድ ሲሆን ሦስትነት እንዳለው፤ ሦስትነት ስላላው አንደ አንድ እንደሆነ ሥላሴም በአካል ሦስት ሲሆኑ በባህርይ በሕልውና አንድ ናቸው፡፡

### መ. የባህር (የቀላይ) ምሳሌነት

የባህር ሦስትነት ስፋቱ ርጥበቱና ሑከቱ (መናወጹ) ነው፡፡ በስፋቱ አብ፣ በእርጥበቱ ወልድ በሑከቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ፡፡

- ይህ ሦስት ከዊን (ሁኔታ) ያለው ባሕር አንድ ባሕር ይባላል እንጂ ሦስት ባሕር እንደማይባል ሁሉ ሦስት ከዊን ያላት ባሕርየ ሥላሴ፣ መለከተ ሥላሴም አንዲት ብትባል እንጅ ሦስት አትባልም

### ሠ. የሦስት ማዕዘን ቅርጽ /Rguilateral Triangle/ ምሳሌነት

በማናቸውም ሁኔታ አንድ ዓይነት የሆኑ ሦስት ጎዎች ጫፍና ጫፋቸው ሲገናኝ ሦስቱም ጎኖቹ ሦስቱም አንግሎቹ እኩል የሆነ ሦስት ማዕዘን /equilateral triangle/ ይገኛል፡፡






ሀ = ለ = ሐ

- ሦስቱ ኅኖች በየራሳቸው ኅን የቆሙ እንደሆነ ሁሉ ሥላሴም በሦስት አካላት፣ በሦስት ገጻት ፍጹማን ናቸው፡፡
- በሦስቱ ኅኖች መካከል የርዝመት የውፍረት ልዩነት እንደሌለ በማናቸውም ነገር እኩል እንደሆኑ ሥላሴም በክብር አንድ ናቸው፡፡
- ከሦስቱ ኅን አንዱ ከሌላ ሦስት ማዕዘን አይባልም እንደዚሁም ሁሉ ከሥላሴ አንዱን ፍጡር የሚል በአምላክ ሕልውና ላይ ምን ያህል የክህደት ትምህርት እንዳስተማረ ከምሳሌው እንረዳለን
- የሦስቱ ኅን ግራ ቀኙ እንዳይታወቅ ለሥላሴም ግራ ቀኝ የላቸውም

*" ተቀዳሚና ተከታይ ቀኝና ግራ የለብንም፣ ጠፈር የለብንም መሠረትም የለብንም ጠፈርም መሠረትም እኛው ነን"*

(ግሩም ቅዳሴ ቁ.)

## ፬ ፯ *ምሥጢረ ሥጋዌ*

### ፬ ፯ ፩ የሰው ልጅ ተፈጥሮና ክብር

እግዚአብሔር ፮ ቀን ሙሉ ዓለምን በሥነ-ፍጥረት እያስጌጠ ካዘጋጀ በኋላ ዓርብ በነግህ " ሰውን በመልካች እንደምሳሌቸችን እንፍጠር" ብሎ ተናገረ፡፡ (ዘፍ ፩፥፳፮)
እንዲህ ተናገረና ግዙፍ አካል ሥጋን ከ ፬ ባህርያት ከመሬት ከውኃ ከነፍስ፣ ከእሳት ከፍሎ አገናኝቶ በሥጋ አለስልሶ በደም አርሶ በጅማት አያይዞ ባጥንት አጽንቶ፣ ረቂቅ አካል ነፍስን ካለመገኛ አስገኝቶ ዕውቀት ቃል ሕይወት ሰጥቶ፣ እነዚህን ሥጋንና ነፍስን አዋሕዶ ሰውን በምሳሌው ፈጠረ፡፡ (ዘፍ. ፪፣፯፤ዘፍ.፩፣፳፯)
ሰው የሚለው በግዕዝ ሰብእ የሚለውን ቃል ነው፡፡ ሰብእ ማለት ፯ ሁኔታ/ጠብይዓት፣ ግብራት/ ያለው አካል ማለት ነው፡፡ የተለየ ስሙን ግን አዳም ብሎ ሰይሞታል /ዘፍ. ፮፥፪/
አዳም በተፈጠረ በ፰ኛው ቀን (በሁለተኛው ዓርብ) "የምትረዳውን የምትስማማውን ረዳት እንፍጠርለት እንጂ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" ብሎ ከአዳም ጎን አንድ አጥንት ወስዶ የምትረዳውን ሴት ፈጠረለት፡፡ (ዘፍ.፪፥፲፰ እና ፳፩-፳፫፤ ኩፋ. ፬፣፬-፯)
አዳምም ከጎኑ ለተገኘች ሴት ሔዋን ብሎ መጠሪያ ስም አወጣላት (ዘፍ. ፫፥፳) ትርጉሙም የሕያዋን እናት ማለት ነው፡፡
ሰው ክቡር ፍጥረት መሆኑ፡-

- በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ በመፈጠሩ
- ከአምላክ በታች በተሰጠው የገዢነት ስልጣን ታውቋል፡፡

(ዘፍ. ፩፥፳፲-፴፤ መዝ. ፰፥፯-፰)

### ፬ ፯ ፪ የሰው ልጅ የተሰጠውን ነፃ ፈቃድና አምላካዊ ትዕዛዝ

የሰው ልጅ ሙሉ ነፃነት ያለው ፍጡር ነው፡፡ ይህም የሚታወቀው በተሰጠው አእምሮ የወደደውን (ክፉውን ከሻተ ክፉውን መልካሙን ከሻተ መልካሙን) እንዲመርጥ **የመምረጥ መብት** የተሰጠው በመሆኑ ነው፡፡ የሚከተሉት ምንባባት ይህን የሰው ልጅን ነፃነት ያሳያሉ

“ተመልከት ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ። በሕይወትም እንድትኖር እንድትበዛም፤ አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት ምድር እንዲባርክህ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድ ዘንድ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ ትእዛዙንና ሥርዓቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝሃለሁ። ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ፤ ብትታለልም ለሌሎች አማልክት ብትሰግድ ብታመልካቸውም ፈጽማችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኂለሁ.... አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖር ዘንድ ሕይወትን ምረጥ.... እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ... ”

(ዘዳ. ፴፥1፮-፳)

“እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እንቢ ብትሉ ግን ብታምጹም ሰይፍ ይበላችኂል”

(ኢሳ. ፩፥1፱)

“ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ”

(ዮሐ.10፥1፮)

እግዚአብሔርም ለአዳም ”ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና” ብሎ አምላካዊ ትዕዛዝ ሰጠው። (ዘፍ. ፪፥፯12)
ይህም አምላካዊ ትዕዛዝ የተሰጠበት ምክንያት፡-

**(፩ኛ) አዳም ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር እንዲገለጥ፡-**

እግዚአብሔር ለአዳም ያለው ፍቅር ከመፍጠር እስከ መግቦት ባለው ተገልጧል። የአዳም ፍቅር የሚታወቀው ደግሞ የፈጣሪውን ሕግና ትዕዛዝ በመጠበቅ ነው።

“ትዕዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለቸው፣ የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው።” እንዲል።

(ዮሐ ፲፬፥፳፩)

ይህንን ትዕዛዝ በማክበር አዳም ከክብሩ ሳይጎድልበት፤ ከጸጋው ሳይቀነስበት ለ፯ ዓመታት እርሱ በእግዚአብሔር ቤት እግዚአብሔርም በእርሱ ልቦና ኖሩ።

“ትዕዛዙን የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም ይኖርበታል” እንዲል

(፩ዮሐ. ፫፥፳፬)

**(፪ኛ) ፍጡርነቱ ይታወቅ ዘንድ**

*ዕፀ በለስ አዳም የሚገዛለት ፈጣሪ እንዳለው የምታሳውቅ የተገዢነት ምልክት ነበረች። አዳም “ሁሉን ግዛ” ቢባልም” ሁሉን ካስገዛለት” በታች መሆኑን ያውቅ ዘንድ አድርግ አታድርግ የሚል ሕግ ተሰጥቶታል።*

**(፫ኛ) ነፃ ፈቃዱ ይገለይ ዘንድ**

*የአንድ ሰው ነፃ ፈቃዱ የሚታወቀው የመምረጥ መብት ሲኖረው ነው። በመሆኑም ለአዳም ሁለት ምርጫ ተሰጠው፤ ሌሎችን ዛፎች ቢበላ በሕይወት የመኖርና ዕፀ በለስን ቢበላ የመሞት ምርጫ። ዕፀ በለስን ባይፈጥርለት ኖሮ አዳም ወደ ፈቅዶ መርጦ መታዘዙን ማወቅ ባልተቻለ ነበር።*

## ፬ ፮ ፫ የሰው ልጅ አወዳደቅ

አዳምና ሔዋን በገነት ፯ ዓመት ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው በሕይወት ከኖሩ በኂላ ሰይጣን በእባብ አድሮ አስቀድሞ ”ለእመ ትበልዑ እንትኮ በለሰ ሞተ ዘትመውቱ” ያላቸውን “ለእመትበልዑ እንትኮ በለስ አኮ ሞተ ዘትመውቱ አላ አማልክተ ትከውኑ” ብሎ አስቷቸው በሉ። የአምላካቸውንም ሕግ ሻሩ። (ዘፍ. ፫፥፩)። ክቡሩ የሰው ልጅ ወደቀ።
አዳም ወደቀ ስንል የሚከተሉትን ማለታችን ነው፡-

- ጸጋው ተገፈፈ
- ባሕርይው ጎስቆለ

**፩ኛ ጸጋው ተገፈፈ**

- **ራቁቱን ሆነ**

አዳምና ሔዋን ለብሰውት ከነበረው በጸጋ ከተሰጣቸው የብርሃን ልብስ ተራቆቱ ፡፡
"የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ እነርሱም ራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ"፡፡ እንዲል፡፡

(ዘፍ. ፫፥፯)

- **ኃይልን አጣ**

አዳም ከበደል በኋላ ፈቃደ ነፍሱ በፈቃደ ሥጋው ላይ የነበራትን ኃይል አጣች፡፡ እንስሳን ይመስል ለመብላት ባማረ፣ ለዓይን በሚያስጎመጅ፣ ለጥበብ መልካም መስሎ በሚታይ ነገር ተሸነፈ፡፡
"ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ፡፡"

(መዝ. ፵፲፣1፪)

ይህ ብቻ ሳይሆን የአምላኩን የፍቅር ድምፅ እንኳ የሚዳምጥበት መንፈሳዊ ኃይልም አጥቷልሽ፡፡
"በገነት ድምፅህን ሰማሁ ዕራቁቴንም ስለሆንኩ ፈራሁ ተሸሸግሁም፡፡"

(ዘፍ. ፫፥፲)

- **እንግዳ ሆነ**

የገነት ባለርስት የዚህ ዓለም ጌታ የነበረው የሰው ልጅ ከበደል በኋላ ይህን ሁሉ አጥቶ እንግዳ ሆነ፡፡
"እኔ በምድር መጻተኛ ነኝና፤ እንደአባቶቼም እንግዳ ነኝ፡፡"

(መዝ. ፴፰፥፲፫፤ ዘፍ. ፵፯፥፰)

**፪ኛ- ባሕርይው ጎሰቆለ**

- **ሰላሙን አጣ**

አዳም ከበደል በኋላ በበህርይው የነበረውን ፍጹም ሰላም አጥቷል፡፡ የኃጢአት ፍጻሜው ሰላምን ማደፍረስ፣ ፈርሃትን ማንገስ ነውና አዳም ኃጢአትን ከፈጸመ በኋላ ‹‹ፈራሁ ተሸሸግሁ›› የሚል ሆኗል፡፡ መጽሐፍ እንዲህ እንደሚል፡፡

" የኃጥእ ሰው ፍርሃት በላዩ ይመጣበታል"

(ምሳ. 1፣፳፬)

"ኃጥእ ማንም ሳያሳድደው ይሸሻል ጻድቅ ግን እንደ አንበሳ ያለፍርሃት ይኖል"

(ምሳ. ፳፲፣6)

- **ሕያውነትን አጣ**

እግዚአብሔር ሰውን በንጹሕ ባሕርይ ያለ ሞት ፈጥሮት ነበር፡፡ ሕያው ፍጥረት አዳም ግን በነጻ ፈቃዱ ተጠቅሞ ‹‹አትብላ›› የሚለውን አምላካዊ ትዕዛዝ በማፍረሱ በነፍስ በሥጋ ሟች ሆነ፡፡ በሥጋው ርደተ መቃብር በነፍሱ ርደተ ሲዖል ተፈረደበት፡፡

- **እግዚአብሔርን መምሰል አጣ**

አምላክ ዘበጸጋ የነበረ ሰው ከአለቆች እንደ አንዱ /ዲያብሎስ/ በኃጢአት በመውደቁ እግዚአብሔርን የመምሰል ክብር አጣ፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት ይህን እንደተናገረ፡፡
"እኔ ግን አማልክት ናችሁ አልሁ፤ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ፡፡ ነገር ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ፡፡"

(መዝ.1፲፣፩፯)

- **ገነትን አጣ**

እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለምና (ማቴ. ፳፪፥፴፪) ሞትን የተሸከሙ አዳምና ሔዋን ከገነት ተባረሩ፡፡

- **ባለዕዳ ሆነ**

ነፃ ፍጥረት የነበረው አዳም ሞትን ያህል ዕዳ ተሸከመ፡፡

## ለአዳም መውደቅ ተጠያቂው ማን ነው?

**፩ኛ የዕፀ በለስ መኖር ነውን**

ዕፀ በለስ ቀድሞውንም የተፈጠረችው ለአዳም መሳሳት ምክንያት እንድትሆን ሳይሆን የአዳም ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅርና ነጻ ፈቃዱ እንዲገለጥባት፣ ፍጡርነቱ እንዲታወቅባት መሆኑን ተመልክተናል። ስለሆነም ዕፀ በለስ መታዘዝንና አለመታዘዝን የምትገልጥ የምልክት ዛፍ ነበረች እንጂ በራሷ ተገዛ መጥታ አዳምን ብላኝ አላለችም፣ በአዳም ላይ ሞትንም ያመጣችው ሞትን የሚያመጣ መርዝ በመያዟ አይደለም።

**፪ኛ ዲያብሎስ ነውን**

ዲያብሎስ ክፉን ምክር መከራቸው እንጂ እጃቸውን ይዞ ዕፀበለስን አላስቆረጣቸውም። አመዛዝኖ መወሰን የእነርሱ ድርሻ ነበር።

ዳያብሎስ ምክንያተ ስህተት እንጂ ስህተት እንድናደርግ የማስገደድ መብት የለውም። እርሱን የመቃወም ሥልጣን አለንና።

> "ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያቢሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተ ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል"
>
> (ያዕ. ፬፥፯)

የሰው ልጅ እግዚአብሔር የታመነ አምላክ እንደሆነ ዕትኖ አውቋል
የዲያቢሎስ ምክር ሁለተኛ ትምህርት ነው። የመጀመሪያው ዕፀ በለስን ብትበሉ ትሞላችሁ እግዚአብሔር ሁለተኛው